

ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት የተጻፉ ብራናው በዚህ መልክ እየተሠራ ነው ።

# ትንሣኤ



« ክርስቶስ በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ የምድር ወገኖች ሁሉ ያዩታል ። መላእክቱ ንም ከታላቅ የመለከት ድምጽ ጋር ይልካቸዋል ። » ማቴ ፳፬ ፡ ፴

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር ፶፩ መጋቢት ፲፱፻፸፬ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ራደ አስረስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


## ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| የጾም ትርጉም በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት | ፪ |
| ክርስቲያን በኅብረተ ሰብእ መካከል | ፫ |
| ክርስቶስ ይመጣል | ፬ |
| መልአከ ገነት ጽጌ ሻውል | ፭ |
| የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ | ፮ |
| በክፉ ክፍለ ሀገር የጊሚራ ብሔረሰብእ | ፯ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፲ |
| የቤተ ክርስቲያን ቅርሶች አሳዛኝነት | ፲፪ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፲፬ |
| ቅርሳችን ይጠበቅ | ፲፭ |
| ትምህርተ ግእዝ | ፲፮ |
| መምህር ግህሉ | ፲፯ |
| የሥጋ ደዌ በሽታ | ፲፱ |
| የሴቶች ምስክርነት | ፳ |
| ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተ ሰቡ የምታስተላልፈው መልእክት | ፳፩ |
| የታመነ ካህን | ፳፫ |


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ያልገባኝን ልጠይቃችሁ?

ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕራፍ ፲፩ ከቁጥር ፳፯-፳፰ "ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት" የሚለው ስላልገባኝ አብራሩልኝ ።

ተማሪ ጥሩነሽ አሸኔ
አሰላ አርሲ

ተማሪ ጥሩነሽ ከሁሉ በፊት በጌታችንና በመድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታችን ይድረስሽ ጥያቄሽ እንደሚከተለው ተመልሶአል ።

"ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላና ይህን ጽዋ የጠጣ ዕዳ አለበት" ማለት በቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ ጊዜ የሚቀርበው ኅብስት የክርስቶስ ሥጋ ወይኑም የክርስቶስ ደም ወደ መሆን እንደሚለወጥ ሳያምን ማንም ሰው ቢቀበል ዕዳ አለበት ማለት ነው ። በተጨማሪም የክርስቶስ ሥጋና ደም የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የዘለዓለም ሕይወትን የሚሰጥ መሆኑን ሳያምን የሚቀበል ዕዳ እንዳለበት ጥቅሱ ያመለክታል ፡ ከዚህም ጋር ቅዱስ ቁርባን የሚቀበል

ሰው ከመቀበሉ በፊት ራሱን ማዘጋጀትንስሐ መግባት ጾም መጾም እንደሚገባው ይኸው ጥቅስ በግልጥ ያሳያል ።

# የሠራተኛ ክርስቲያን ጾም

ከቄ/መክብብ አጥናው

ከዕንቁላል ከወተት ከሥጋ እየጾሙ
ባልኮሆል ተሳክረው ስድብ እያሸከሙ
አምባጓሮ ፈጥረው ሰው የሚያስቀይሙ
የያሬድን ትርጉም አልሰሙ እንደሁ ይስሙ፡-

ሥራን ለመበደል ደባ ከመሥራት
ክፉ ከመናገር ክፉም ከማየት
አፍ ይጹም ዐይን ይጹም ይጠብቅ ሥርዓት
ጆሮም እንኳ ይጹም ክፉ ከመስማት
አሉባልታ በዝተዋል ይቅርብን ሐሜት
መላው ሕዋስ ይጹም ክፉ ከመሥራት
ማንም የሚያምንበት ይህ ነው ጾም ማለት ።

መሠረት በሌለው በከንቱ አሉባልታ
የስንት ባለትዳር ቤት ንብረት ተፈታ
ስለዚህም ይላል የቅኔው ወዳጅ
ቡና መልካም ነበር ለሱስ የሚበጅ
ቁርሱ "የሰው ሥጋ" መሆኑ ነው እንጅ ።

በጠለፋ ወሬ የሰው ስም በማጥፋት
በሐሜት ቢላዋ የሰው ሥጋ መብላት
ይህ ነው አንዱ ክፍል ግድፈተ ጾም ማለት
ሐሜት ወረርሽኝ ነው ብርቱ ተላላፊ
አሉባልታ እባብ ነው ሥውር ተናዳፊ
ስለዚህም አለ የቅኔው ጸሐፊ

ጋሬጣና አሽሟጣጭ አንድ ነው ባሕርያቸው
የሚያልፈውን ሁሉ በመቦጨቃቸው ።

እንዲህ ስለተባለ ግን ሐሜት ተናጋሪውን
ያቀልላል እንጂ የሚታሙትን
ይጐዳል ማለት አይደለም ።

ይህን ሲያስረዳ ፈላስፋው አሪስቶትል ሰዎች ያሙሃል ብለው ቢነግሩት «እንኳን ማማትና በሌለሁበት ቢደበድቡኝም ግድ የለም ልሙት" ሲል መለሰላቸው ይባላል ።

መጾም የሚገባን ከምግብ ብቻ ሳይሆን ከክፉ ነገርም ጭምር መሆኑን አንዘንጋ ።

በተለይም ክፉ ከሆነው ከብርቱ አልኮሆል መጠጥ ጭምር መጾም ቢቻል እንዴት መልካም ነበር ! ለዚህም የሁለት ባለቅኔዎችን ግጥሞች መደምደሚያ አድርገን እናቀርባለን ።

1 ዝሙትና ውሃ ሰው ጠልፈው ሲወስዱ
እያሳሳቁ ነው ቁልቁል የሚወርዱ ።
ሊቀ. ማ.(አበባው ይግዛው)

2 የሰው ልጅ ሞኝ ነው አንጐሉ ፈዛዛ
ወተት እየሸጠ አረቄ እሚገዛ
አልኮል አትጠጣ ወተት ይሻልሃል
አልኮል ብትጠጣው ምን ይጠግንሃል
ጓያ እንደሰበረው ያሽመደምድሃል ። (ቄ. ዳኛቸው ካሣሁን)



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

## የጾም ትርጉም በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት

ጾም ራሳችንን ለእግዚአብሔር የምናስገዛበት ታዛዥነትንም የምንገልጽበት መሆኑን እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊያውቀውና ሊረዳው ያስፈልጋል ።

ጾም ከጥሉላት መከልከል ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ የሰው ልጆችን ከሚጐዳ ክፉ ነገር ሁሉ መከልከል ለሌሎች በጐ ሥራን ማድረግ ይጠይቃል ።

በማንኛውም የሃይማኖት ሥርዓት ጾም መኖሩ ቢታወቅም የጾሙ ሥርዓት ይለያያል ዕብራውያን ሲጾሙ ውለው ማታ ጥሉላት እንደሚበሉ ከአንዳንድ ሊቃውንት ተረድተናል ግን የጾማቸው ዋና ዓላማ ከጧት እስከ ማታ ከማንኛውም ምግብ መከልከል ሥራ አለመሥራትና በጸሎት ቤታቸው መዋል ነው ።

በክርስትና እምነት ተከታዮች ከዕብራውያንና ከሌሎች ሃይማኖታውያን ጾም የተለየ ሥርዓት ይታያል ። እስከ ተወሰነ ሰዓት ከተወሰነ ምግብ መከልከል የጾሙ ሳምንታት እስኪፈጸሙ ድረስ ከጥላሎት ብቻ ሳይሆን ሰውን ከሚጐዳ ነገር መጠበቅን ይፈልጋል ።

በተለይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የዓቢይ ጾም ሳምንታት ስምንት ከመሆናቸውም በላይ በእነዚህ ሳምንታት ጥሉላት መብላት ክልክል ነው ። የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ግን እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን በተለየ መንገድ ይጾማሉ ።

የሩሲያን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጾም በመጀመሪያው ሳምንት ሥጋ አይበላም ፣ ሁለተኛው ሳምንትም እንደ ስሙነ ሕማማት መጾሙን ተረድተናል ፣ ሌሎችንም ሳምንታት ይጾማሉ ፣ በሌሎች ምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ከቅድስት ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ሳምንታት በጥልቅ ስሜትና በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት እንደሚጾሙ ይነገራል ።

መቼም ጾም ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት መሆኑን ገልጸናል ። በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትም የጾሙ ሥርዓት እንዴት እንደሚለያይ በመጠኑ አቀርበናል ።

ግን የጾሙ ትርጉም በክርስቲያኖች ዘንድ አንድ ዓይነት መልክ እንዲኖረው ከተፈለገ በየአብያተ ክርስቲያናት ያለው ሥርዓተ ጾም አንዱ ፣ አንዱን ሳይነቅፍ ፣ እንደተጠበቀ ሆኖ ክርስቲያኖች ለቁርስ የሚያደርጉት ወጭ ተጠራቅሞ ለአንድ ዓይነት ሥራ ቢውል እንኳን የጾም ትርጉም በታወቀ ነበር ።

ምናልባት የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እምነት ተከታዮች ችግረኞችን በመርዳት የሃይማኖት ድርጅቶቻቸውን በማስፋፋት ይህንን በተግባር እንደሚያውሉት በመገናኛ ዘዴዎች ሰምተናል ተረድተናል ።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮችም ቢሆኑ ከአንዳንዶች በቀር ሥርዓተ ጾሙን በትክክል ሲጾሙ አይታዩም ።

ሌላው ደግሞ በጾም ጊዜ የሚካሔደው የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት አንዲ ቤተ ክርስቲያን ስትቀድም ሌላዋ ስትዘገይ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች የሥነ ሥርዓት አለመስተካከል ልዩነት ስለሚፈጥር የሚመለከተው ክፍል አንድ ዓይነት መመሪያ ቢያስተላልፍ የቅዳሴው ሥነ ሥርዓትና ጾሙ እንደሚስተካከል ግልጽ ነው ።

በመሠረቱ በከተማ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት መግቢያና መውጫ ብቻ ልዩነት እንመለከት ይሆናል ፣ በተለይ በገጠሩ ኢትዮጵያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ግማሾቹ በስምንት ሌሎቹ በዘጠኝ ስለሚገቡ የጾሙ ሰዓት የተወሰነ ሆኖ አይታይም ።

ምናልባት በገጠሩ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ያሉት ካህናት የሚተዳደሩት በግብርና በመሆኑ ቀድሰው ወደ ሥራ መሠማራት ስለማይችሉ ነው የሚል አስተሳሰብ ይኖረን ይሆናል ። ይህም ቢሆን ሰዓቱ የተወሰነ ካልሆነ ምእመናንን ግራ ስለሚያጋባ በአንድ ዓይነት ሥርዓት ሊመሩና ቤተ ክርስቲያናቸውን ሊያገለግሉ አይችሉም ።

እንግዲህ የጾም ትርጉሙ ከሚመጣው ችግር ለመዳንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማወቅ መሆኑን አምነን ጾማችን እንደ ግብዞች ለይስሙላ አይሁን በጾም የምንቆጥበውን ገንዘብም ለችግረኞች እናውለው የጾም ትርጉሙ ገንዘብን አጠራቅሞ ለፋሲካ እንዲውል ማድረግ አይደለምና ።



# ክርስቲያን በኅብረተ ሰብእ መካከል

ክርስቲያን ከኅብረተሰቡ ሳይለይ በኅብረተሰቡ መካከል ይኖራል ። ኅብረተ ሰቡን ከሚጐዳ በእግዚአብሔርም ፊት ኃጢአት ሆኖ ከሚቆጠር ነገር በቀር ኅብረተሰቡ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ይሠራል ። በሚሠራውም ሥራ ለኅብረተሰብእ መልካም ምሳሌ ሆኖ መኖር እንደሚገባው ለክርስትና ሕይወት መመሪያ የሆነው መጽሐፍ ያስረዳል ። “በቃልም በኑሮም፡ በእምነትም በንጽሕናም ምሳሌ ሁን” በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ትእዛዝ ማንኛውም ክርስቲያን ለሌሎች ጥሩ ምሳሌ መሆን እንዳለበት ያመለክታል።

ምሳሌነት በቃል ብቻ አይደለም ። በተግባርም ነው እንጂ ። ስለዚህ ክርስቲያን በኅብረተ ሰብእ መካከል በሚከተሉት ሁኔታዎች ምሳሌ መሆን ይችላል ።

፩ኛ ክርስቲያን ለሚኖርባት ሀገር ጥሩ ዜጋ መሆን ይገባዋል ። ጥሩ ዜጋ ሀገሩን ይወዳል ። ስለ ሀገሩ እውነተኛ ታማኝነቱን ይገልጣል ። ሀገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ በረከት ሆና የተሰጠችው መሆንዋን አስተውሎ ይንከባከባታል ። ከጠላት ይጠብቃታል። ዳር ድንበርዋን ያስከብራል ። ለእድገትዋና ለልማትዋ በአለው ችሎታ ተግቶ ይሠራል ፣ የሀገሩን ሕገ መንግሥት ያከብራል ። በሕብረተሰቡ መካከል ለሕግ መፍረስ ምክንያት አይሆንም ። ሕግ አፍራሾችንም አይከተልም ። ቅዱስ መጽሐፍም ክርስቲያን በሕገ እግዚአብሔርና በሕገ ሰብእ መኖር እንደሚገባው ያስተምራል (ሮሜ ፲፫፡፩-፯)። እርግጥ ስለ ሀገር የሚደረግ ታማኝነትና ሀገር ወዳድነት በሀገር ውስጥ ኢርቱዕ ፍትሕን አድልዎን ጭቆናን የሃይማኖት የዘርና የጾታ ልዩነትንና ኢሰብአዊ ድርጊትን ከመቃወም አያግድም ። እግዚአብሔር ለማንም አያዳላም፣ ሁሉም በእግዚአብሔር ዘንድ እኩል ነው ። በዚህ አንጻር ክርስቲያን ለሀገሩ ጥሩ ዜጋ እንደመሆኑ መጠን በዘርና በጎሳ በሌላውም ነገር ሁሉ አድልዎ አያደርግም ፣ ማድረግም አይገባውም ። በእርሱ ዘንድ ሁሉ እኩል እንዲሆን ይገባል ። “ሰማያዊ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ” ተብሎአልና ።

ክርስቲያን ሁልጊዜ የክርስቶስን ትምህርትና ምሳሌነት መከተል እንደሚገባው የስሙ ትርጉም ያስረዳል ፣ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብሎ ተጠርቶአልና አንድ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግብር እንዲከፍል ተጠይቆ ከፈለ ፣ (ማቴ. ፳፪፥ ፲፱) ክርስቲያን ተገቢውን ግብር ብቻ ሳይሆን ለሀገር በሚያስፈልገው ሁሉ በፈቃዱ ባለው ኃይልና ገንዘብ ይረዳል ። በጠቅላላ እስከ ደም ጠብታ ድረስ መሥዋዕት ይከፍላል ። ይህንም ጥሩ ዜጋ እንደመሆኑ መጠን በደስታና በሀገር ወዳድነት ይፈጽማል ። ሀገርን መውደድ ሃይማኖትን አይከለክልም ። እግዚአብሔርን ማምለክም ሀገርን ከመውደድና ለሀገር መሥዋዕት ከመሆን አያግድም ።

ክርስቲያን ጥሩ ዜጋ ከመሆኑ ጋር ሥነ ሥርዓታዊ ስለሆነ በግብረገብነቱ ለኅብረተሰቡ ታላቅ ጥቅምን ይሰጣል። በክርስቲያንነቱ ስለ ሀገሩ ይጸልያል፡ (ኤር. ፳፱፥፯) ባለው ችሎታ በቅንነትና በታማኝነት ይሠራል ። ኅብረተሰቡ ሁሉ ስለ ሰላም ስለ ሀገሩ ፍቅርና ስለ ሕግ አጠባበቅ በጠቅላላ ሀገርን በሚመለከት ጉዳይ ሁሉ ጥሩ ዜጋ ይሆን ዘንድ የጥሩ ክርስቲያን ምሳሌነት ለኅብረተሰቡ ያገለግላል ።

፪. ክርስቲያን በበጎ አድራጎት

ክርስቲያን በዘርና በሃይማኖት ልዩነትን ሳይፈጥር ለሁሉም መልካም እንዲያደርግ ተጠርቶአል (ገላ. ፮፥፲) በድካም ከሚያገኘው በረከት ሁሉ ለሌሎች ያካፍላል ። ድሃ አደጎችን ሕመምተኞችን ስደተኞችን እሥረኞችን ፣ ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን በተቻለው መጠን ለመርዳት ኃላፊነት እንዳለበት ክርስቲያን ያስተውላል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ስለዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ይናገራል ። “ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው ። ወላጆች የሌሉአቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለም ም ከሚገኝ እድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው ፣ (ያዕ. ፩፥፳፯) ። ይህም የክርስቲያን እምነት በተግባር መገለጥ እንዳለበት ያሳያል ።

በዓለም ውስጥ የርዳታ ኃይል የሚያስፈልጋቸው ብዙ ክፍሎች አሉ ። ለምሳሌ ወላጆች የሌሉአቸው ልጆች ጠዋሪ የሌላቸው ሽማግሎችና ባልቴቶች ራሳቸውን ለመርዳት የሚያስችል ጉልበት ወይም ዕውቀት የሌላቸው በልዩ ልዩ ደዌ አካላቸው የጐደለባቸው እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ ሁሉ የሌሎች በጎ አድራጎት ያስፈልጋቸዋል ። ክርስቲያን እንደዚህ ባለው ኅብረተሰብ መካከል ሲኖር በጉልበቱ ፣ በገንዘቡና ፣ በዕውቀቱ ይረዳል ። ራሱ መርዳት ባይችል እንኳ ለሚችሉ ኃያላት ያመለክታል ።

ከእነሱም ርዳታውን ተቀብሎ ለችግረኞች በታማኝነት ያካፍላል ። ታማኝነት ከክርስቲያን የሚጠበቅ ምሳሌነት ነውና ።

፫. ክርስቲያን በአድልዎ (በትክክለኛነት)

በአሁኑ ጊዜ በማንኛውም ኅብረተ ሰብ ውስጥ ጐልተው ከሚታዩ ችግሮች መካከል አንደኛውና ዋናው በዘርና በጎሳ ፣ በወዳጅና ፣ በዘመድ ምክንያት ልዩነት በመፍጠር የሚደረገው አድልዎ ነው ። ከዚህ ደዌ ጤናማ የሆነ ክርስቲያን እውነተኛ ክርስቶሳዊ እርሱ ነው ። በእርግጥ ክርስቲያን ከአድልዎና ልዩነትን ከማድረግ ይከለከል ዘንድ

ወደ ገጽ ፳ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቶስ ይመጣል



ክርስቶስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ

አዳምና ሄዋን በስሕተታቸው ከምድረ ገነት ወጥተው ተባረው በፍዳና በመርገም ከወደቁ ወዲህ እግዚአብሔር አምላክ ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር ።

ተስፋውም ወደዚህ ዓለም መጥቶ የእነርሱን ሥጋ ለብሶ ከተወ ለደ በኋላ ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሎ ሞቶ ተነሥቶ ከወደቁበት ፍዳና መርገም ነጻ እንደ ሚያወጣቸው የሚያረጋግጥ ነበር ። ይኸው የተነገረው የተስፋ ቃል ያለ ጥርጥር እንደሚፈጸምም በየጊዜው የተነሡ ነቢያት በትንቢታቸው እያረጋገጡ አለፉ የተነገረው ትንቢት የተቆጠረው ሱባኤ በተፈጸመ ጊዜ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ ተወለደ ይህንንም ሐ. ጳውሎስ በመልእክቱ ሲያረጋግጥ "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ"' ብሏል ገላ. ፬ ፡ ፬ ።

ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ ቀስ በቀስ አድጎ በ፴ ዘመኑ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ለሦስት ዓመት ያህል እየዞረ ወንጌልን ካስተማረ በኋላ በቀራንዮ አደባባይ ራሱን በመስቀል ላይ በመሠዋት በፍዳና በመርገም ተይዞ በመንጸፈ ደይን ወድቆ ሲጨነቅ የነበረውን የሰው ዘር ሁሉ በጠቅላላ ነፃ አወጣው ። አምላክ የአምላክ ልጅ ይመጣል የሰውን ልጅ ነፃ ያወጣል እየተባለ የተነገረው ቃል ሁሉ ስለተፈጸመ የመጀመሪያው ተስፋ በዚህና ይህንን በመሰለ መንገድ ተፈጽሟል ።

ወደፊት የሚጠበቀው ሁለተኛ መምጣቱ ነው ክርስቶስ ሁለተኛ እንደሚመጣ በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጿል ።

ክቡር ዳዊት "እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል አምላካችን ይመጣል መጥቶም ዝም አይልም እሳት በፊቱ ይቃጠላል በዙሪያውም ብዙ አውሎ አለ በላይ ያለውን ሰማይን በታች ያለችውንም ምድርን ይጠራል በሕዝቡ ለመፍረድ" ሲል ተናግሯል መዝ. ፵፱ ፡ ፪

የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ከመጀመሪያው የተለየ ይዞታ አለው ። የመጀመሪያው አመጣጡ ስለሰው ልጆች በደልና ኃጢአት ለመሠዋትና እነርሱንም ከፍዳና ከመርገም ለማዳን ነበር ሁለተኛ ምጽአቱ ግን መልካም ለሠሩ ዋጋቸውን መንግሥተ ሰማያትን ክፉ ለሠሩ ደግሞ ፍዳቸውን ለመክፈል ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለዕብራውያን በጻፈው መልዕክቱ ላይ ሲገልጽ "አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጧል ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላ ፍርድ እንደተመደበባቸው እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል ብሏል ዕብ ፱. ፳፮ - ፳፰ ።

እንዲሁም ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ተግባር አከናውኖ ወደ ሰማያዊ ዙፋኑ በሚያርግበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ እጅግ በጣም በመደነቅ በመደንገጥ ትኩር ብለው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ ሁለት መላእክት በሰው አምሳል ነጫጭ ልብስ ለብሰው አጠገባቸው ቆሙና "እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ!! ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የአረገው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ እንዳያችሁት እንዲሁ ተመልሶ ይመጣል" በማለት ክርስቶስ ሁለተኛ ተመልሶ የሚመጣ መሆኑን ስላስረዷቸው ወደሚኖሩበት ቦታ ተመልሰዋል የሐ. ሥራ ፩. ፲-፲፪።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሰው ሆኖ ባስተማረበት ጊዜ ሁለተኛ እንደሚመጣ ሕዝቡን ሲያስተምር የሚመጣበትን ዕለቱን ወርሁን ለማወቅ ስለፈለጉ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀረብ አሉና ንገረን ሁለተኛው መምጣትህ መቼ ይሆናል የመምጣትህስ ምልክት ምንድን ነው? የዓለሙስ መጨረሻ ምን ጊዜ ነው? በማለት ጠየቁት ።

ክርስቶስ ለጥያቄያቸው መልስ ሲሰጥ "ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰማላችሁ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣልና ፣ ረኃብ ቸነፈር የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች በማለት ሁለተኛ መምጣቱ ሲቃረብ የሚፈጸሙትን ምልክቶች ከተናገረ በኋላ ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር የሰማይ መላእክት ቢሆኑም የሚያውቅ የለም ሲል የደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ ዘግቶታል ማቴ. ፳፬. ፫-፭ ፡ ፲፪-፴፮ ።

ክርስቶስ ሁለተኛ ሲመጣ ስለሚፈጸሙት ድርጊቶች ወንጌላዊው ማቴዎስ በጻፈው ክፍለ ወንጌል ሲገልጽ "የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል ይልና ጻድቃንን በበጎች ኃጥአንን በፍየሎች መስሎ ገልጾ ጻድቃንን በምድር ሳሉ ስለሠሩት መልካም ሥራ አመስግኖ ወደ ዘለዓለም ደስታ ኃጥአንን በክፉ ሥራቸው ወቅሶ ወደ ዘለዓለማዊ ሥቃይ እንዲሄዱ ይናገራል ማቴ. ፳፭. ፴፩ - ፵፯ ።

የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ "ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ ኃጢአተኞችንም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም በእርሱ ላይ ስለተናገሩ ስለ ጭካኔ ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፍ ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል" ብሎ ትንቢት ተናግሯል ሲል በመልእክቱ ጠቅሶአል ይሁዳ ፩. ፲፬ - ፲፭ ።

የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት መልካም ለሠሩ ደስታ ክፉ ለሠሩ ፍዳ መሆኑን ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ሲናገር "በመቃብር ያሉት ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይነሣሉ" ብሏል የዮሐ. ወንጌል ፭. ፳፱ ።

ሐዋርያው ዮሐንስ በራዕዩ ሲገልጽ "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ አልፋና ኦሜጋ ፊተኛና ኋለኛ መጀመሪያና መጨረሻ እኔ ነኝ ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው" ይላል ራዕየ ዮሐ. ፳፪.፲፪፡

ቅዱስ ያሬድም በዳግም ምጽዓቱ ይትፌሥሐ በመንግሥቱ አለ አምኑቦቱ" በሁለተኛው አመጣጡ ያመኑበት ይደሰታሉ ብሏል ።

የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት በተቃረበ ጊዜ ይፈጸማሉ ተብለው ከተነገሩትም ምልክቶች ጥቂቶቹ በመፈጸም ላይ ናቸው ። ስለዚህ ክርስቶስ ሁለተኛ በመጣ ጊዜ የማታልፈውን መንግሥቱን ለመውረስ እንበቃ ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት አጽንተን ሥነ ምግባራችንን አሳምረን እንኑር ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

---

# ክርስቲያን በኅብረተሰብእ...

ከገጽ ፫ የዞረ

መጽሐፍ እንዲህ ይላል "በክርስቶስ አይሁዳዊ የለም ። ግሪክ የለም ፣ ድሀ የለም ፣ ሀብታም የለም ፣ ሴት ወይም ወንድ የለም ። ሁሉ በክርስቶስ ዘንድ አንድ ነው ። እኩልም ነው ። ሁሉም በእምነት የእግዚአብሔር ልጆች የክብር ተካፋዮች ሆነዋል ።»

ክርስቲያን ሁሉን በክርስቶስ ዓይን ሊመለከት ይገባዋል ። በክርስቶስ ዓይን ማየት ሲችል የዘርና የቀለም የጐሳም ልዩነት አያደርግም ። ግን ሁሉንም እንደ ፍጥረተ እግዚአብሔር ያያል ። ለሁሉም በእኩልነት ያስባል ። በእውነት የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሁሉ ራሱ አድልዎ ካለማድረጉም በላይ ሌሎች አድላውያንን ይገስጻል ፣ እውነትና ርቱዕ ፍትሕ በኅብረተሰብ መካከል እንዲበዙ ታላቅ ጥረት ያደርጋል ። በተግባርም ይገልጣል ።

ክርስቲያን ፊት አይቶ ወገንና ሥልጣን ፈርቶ ማን አለብኝ በማለትም በራሱ ኃይል ተመክቶ አድልዎ እንዳያደርግ በእግዚአብሔር ቃል ታዝዞአል ። "ኢታድሉ ለገጸ ሰብእ - የሰው ፊት አይተህ አታድላ" ይላልና ቃለ እግዚአብሔር ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ





www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## መልክአ ገነት ጽጌ ሻውል

በከፍተኛ ሊቅነታቸው ስመጥር የነ
በሩት መልአከ ገነት ጽጌ ሻውል በሸዋ
ክፍለ ሀገር በመርሐ ቤቴ አውራጃ ልዩ
ስሙ አፈዘዝ በሚባል አካባቢ በ1972
ዓ.ም. ጥር 15 ቀን ተወለዱ ።

በተወለዱበት ቦታ በአምስት ዓመ
ታቸው ዳዊት ደግመው እንደጊዜው
ባህላዊ ይዘት ከወላጆቻቸውና ከቤተ
ዘመዶቻቸው ልዩ ልዩ የሆነ የምሥራች
ስጦታ ተቀበሉ ፤ ቀጥሎም የአሥራ አራ
ቱን ቅዳሴያት ዜማ ተምረው በወቄና
በዚያው ደን አቦ በተባለው አካባቢ ከ
አለቃ ዜና ቅኔ ከነአገባቡ በሚገባ አጥ
ንተው ለመምህርነት በቁ ።

ቀጥሎም በወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሜዳ
ከሚገኙት ከታላቁ ሊቅ ከመምህር አካ
ለ ወልድ ዘንድ ሔደው የታች ቤቱን
ትርጓሜ ሐዲሳት ሊቅ መምህር ወልደ
ሚካኤልን በአጋጣሚ ከዚያው ስለአገ
ኙዋቸው ከጉባኤያቸው ሐዲሳትን ተም
ረውና አደላድለው ካወቁ በኋላ ወደ
መምህር አካለ ወልድ ጉባኤ ተዛው
ረው የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትር
ጓሜ ተማሩ ።

የሊቅነታቸውና የተመራማሪነታቸ
ውም ተቅዋም መጠናከር በብዙዎች
ዘንድ ስለተገመገመ በመምህር አካለ
ወልድ አማካይነት በራስ ወሌ ተጠይ
ቀው በመርጦ ቅዱስ ሚካኤል ደብር
የቅኔና የትርጓሜ መጻሕፍት ጉባኤያቸ
ውን ዘርግተው እንዲያስተምሩ ተደርጎ
በቂ መተዳደሪያ ተሰጥቶዋቸው የትም
ህርት ፋና ያበሩበት በነበረው በዚሁ
ጉባኤያቸውም ብዙዎች ሊቃውንትን
በዕውቀት በማጎልመስ ለኢትዮጵያ
ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ አስተዋፅኦ
አበርክተዋል ።

ለሦስት ዓመታት ያህል በመርጦ ካስ
ተማሩ በኋላ ትምህርትን በየቅጣጫው
ለማጠናከር ብርቱ ፍላጐት ያለው ህሊ
ናቸው ስለቀሰቀሳቸው ለጊዜው የማ
ስተማር ተግባራቸውን አቁመው
ብሉያትን ለመማር ወደጐጃም ክፍለ
ሀገር ይሄዱ ዘንድ ራስ ወሌን ፈቃድ
ቢጠይቁ ከዚሁ ከቅርቡ ከመምህር አካ
ለ ወልድ ዘንድ ተመልሰው ትምህርት
ዎን ይቀጥሉ እንጂ ወደጐጃም ሊሄዱ
አይችሉም ብለው አሳባቸውን ገቱባ
ቸው ።

ሊቁ የራስ ወሌ ትእዛዝ ወሳኝ መስሎ
ስለአልታያቸው በሥውር ጓሳ አምባማ
ርያም ወደሚባል ቦታ ሄደው የሐዲሳት
ን ትርጓሜና ቅኔ ለሁለት ዓመታት ያህ
ል አስተማሩ በዚህም ወቅት አለቃ መን
ክር የተባሉት የሐዲስ ትርጉም ደቀ
መዝሙራቸው አቋቋም ያውቁ ስለነ
በሩ ከእርሳቸው አቋቋምን ተምረዋል ።

መልአከ ገነት ጽጌ በዜማ ትምህርት
ፍቅርና ጣዕም በጣም ስለተቀሰቀሱ
በጐንደር ክፍለ ሀገር በጋይንት አው
ራጃ እየተዘዋወሩ ተጉለቱ የነበረ
ውን የዜማ ትምህርታቸውን ቤተ
ልሔማዊ ዜማ አድርገውታል ።

የዜማ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ
በኋላ በጐጃም ክፍለ ሀገር ወደሚገኘ
ው ወደሞጣ ጉዞዋቸውን ቀጥለው በብ
ሉያት ትርጓሜ ሞያቸው እጅግ አድር
ገው ይመሰገኑ ከነበሩት ከርእሰ ደብር
ካሣ የአርባ ስድስቱን መጻሕፍተ ብ
ሉያት ትርጓሜ ተማሩ በዚህም ጊዜ ለአ
ስተማሪያቸው ርዕሰ ደብር ካሣና ለሌሎ
ችም የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ አስተ
ማሩ ።

የብሉያትን ትርጓሜ በሚገባ አደላድ
ለው በመምህርነቱ መድረክ ላይ ለመ
ቆም በነበራቸው ዕቅድም በደብረ ወር
ቅ ወደነበሩት ወደመምህር ሰው አገኝ
ሁ ዘንድ ሔዱና ብሉያትን በሚገባ ዐው
ቀው ጽፈው ከመምህራቸው ተሰናብ
ተው ለመሄድ ሲነሱ አባ ወልደ ሥላሴ
የተባሉ የአሥራ አራቱ ቅዳሴያት ትር
ጓሜ መምህር ብሉይ ለመማር ከመም
ሀር ሰው አገኘሁ ዘንድ ስለሄዱ መል
አከ ገነት በዚህ አጋጣሚ ተደስተው
የቅዳሴያትን ትርጓሜ በሙሉ አጠናቅ
ቀው ተማሩ ።

በዚህም ጊዜ በትምህርት ታታሪነታ
ቸውን ተጨባጭ ሁኔታቸውን ቢታሪክ
ገምጋሚዎች ቀደም ብለው የተረዱት
ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ወደአዲስ አበባ ከ
ተማ እንዲመጡ የጥሪ ደብዳቤ ስለአስተ
ላለፉላቸው በግል የነበራቸውን መ
ርሐ ግብር ትተው ወደ አዲስ አበ
ባ መጡና የወር ደመወዝ ተመድቦ
ላቸው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብ
ር ሆነው እንዲያስተምሩ ተደረገ ።

በዚሁ ደብር ለስድስት ዓመታት ያህ
ል ብሉያትን ፣ ሐዲሳትን ፣ መጻሕፍተ
ሊቃውንትንና ቅኔ ሲያስተምሩ ከቆዩ
በኋላ በልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት
በሊቅነታቸው ተመርጠው በአጠቃ
ላይ የመንግሥት ፍርድ አደባባይ ፍት
ሐ ነገሥት አውጭ ሆኑ ።

በዚህም ወቅት ግብፃዊው የኢትዮ
ጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ
ሊቅነታቸውን በቅርብ ስለተገነዘቡት
ከመንግሥት አስፈቅደው ለመታሰቢያ
ቸው ያሳነፁት የመናገሻ ቅዱስ ማርቆስ
ደብር አስተዳዳሪ ሆነው የትምህርት
ጉባዔያቸውን እንዲያስፋፉ በማድረጋ
ቸው በመናገሻ ቅ/ ማርቆስ በማስተማር
ብዙ ደቀ መዛሙርት አፈሩ ።

በመናገሻ ቅዱስ ማርቆስ በማስተዳ
ደርና በማስተማር ሁለት ዓመታት ከቆ
ዩ በኋላ በዚያን ጊዜ ስመ አጠራር በአ
ዲስ አበባ መካነ ሥላሴ አሁን መንበረ
ፀባዖት መልአከ ብርሃን ተብለው ተሾ
ሙና እያስተማሩ ደብሩን ለአሥራ ሁለ
ት ዓመታት ያህል አስተዳደሩ ።

ቀጥሎም መልአከ ኃይል ተብለው
የእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ደብር አስተዳ
ዳሪ ሆነው ከቆዩ በኋላ ግፈኛው ጠላት
ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በኢትዮ
ጵያ ሊቃውንት ተመርጠው ለረጅም
ጊዜ ባስተማሩበት በመናገሻ ቅዱስ
ጊዮርጊስ ደብር መልአከ ገነት ተብለው
ተሾሙና ለሁለት ዓመታት በአስተዳዳ

ወደ ገፅ ፱ ዞሯል



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## የድርሰት ፈለገ ሕይወት

በኮሜዲም ሆነ በትራጀዲ መልክ በ
ሚሊዮን የሚቆጠሩ መጻሕፍት ተደርሰ
ዋል ዕልፍ አዕላፍ የቅኔ ዓይነቶች ታሪ
ክና ምሳሌዎች ያልተዘሩበት ክፍት ቦ
ታ በዓለም ውስጥ አይገኝም ፤ ታዲያ በ
ሚሊዮን ከሚቆጠሩ ዕልፍአዕላፍ መጻ
ሕፍት መካከል የብዙዎች መሠረትና ዋ
ና ምንጭ የቅዱሳት መጻሕፍት ታሪካ
ዊ ፅንሰ ሐሳብ ነው።ይኸውም ያለምክ
ንያት አይደለም ።

ለምሳሌ ቅዱሳት መጻሕፍት

፩- የቅኔ ጥበብ መንገዶችን መርሕ በ
የዓይነቱ ያቀርባል

፪- የታሪክና ምሳሌዎች የንግግርም
ጥበብ በየመልኩና በየዓይነቱ
ተንፀባርቆበታል

፫- ውበት ያለውን የሐሳብ አገላለጥ
ቴክኒክ በየዓይነቱ ያቀርባል

፬- የታሪክና የሕግጋት ምንጭ ነው

፭- የኢያንዳንዱን ኅብረተሰባዊ ዕድገ
ት ወይም ሥርዓተ ማኅበርና
ሥነ መንግሥት ሁሉ ባጭር ባጭ
ሩ ይጠቁማሉ

፮- ከብረት የጠነከረ ሥነ ሥርዓት
ከጥሩ ምግባር የሞራል የትምህ
ርት ጋር ያቀርባል

፯- ሁል ጊዜ አዲስ የሆነ ውብ የሥ
ዕላዊ ንግግር ጥበብ ይታይበታል

፰ ኮሜዲና ትራጀዲ የሆኑ የድርሰት
መንገዶች መሠረታዊ ንድፈ ሐሳብ
ይገኝበታል

፱- ለኅሊና በሚሰማ ሁኔታ የሚያቀ
ርበው መልእክት ቃሉና ፍሬ ነገሩ ም
ን ጊዜም የማይበርድ ስለት ነው
ማለት ይቻላል ለዚህም ማስረጃ
ዝርዝር ውስጥ ስንገባ በተለይ
ከቅኔ መንገዶች ጥቂቶችን እንጠቁማለ
ለን

### የቅዱሳት መጽሐፍት ቅኔዎች መንገድ

ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራእየ ዮሐን
ስ አልፎ አልፎ የተዘሩ ብዙ ቅኔዎች አ
ሉ ። በተለይም ። ፩ መጽሐፈ ኢዮብ
፪/ መዝሙረ ዳዊት ፫/ ምሳሌ ሰሎሞን
፬ መክብበ ሰሎሞንና ፭ መኃልየ መ
ኃልይ ዘሰሎሞን የተባሉት ክፍሎች የ
ቅኔ መጻሕፍት ተብለው ይጠራሉ

አስደናቂው ቁም ነገር ደግሞ የቅዱ
ሳት መጻሕፍት ቅኔዎች ወደየትኛው
ም ቋንቋ ቢተረጐሙ ውበታቸው አይለ
ወጥም ። ዋጋቸው አይቀነስም እስካሁ
ን በ፩ሺህ ፺፪ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል

### አስረ ሰምና ወርቅ ወይም ንዕዕር የቅኔ መንገድ

በመሠረቱ ንዕዕር የተሠኘው የቅኔ መ
መንገድ አንድን ነገር ከሌላው ጋር በማ
መሳሰልና በማወዳደር ምሥጢር
ን እያጐላ የሚገልጥ ግጥም ወይም ዐረ
ፍተ ነገር ነው ። ከሠምና ወርቅ የሚለ
ይበት መንገድ ብዙ አይደለም ። ሁለቱ
ንም ማለት ንዕዕርና ሠምና ወርቅ ከተ
ሠኙት ቅኔዎች ጥቂቶቹን በኦሪት ዘፍጥ
ረት ፵፱ ፣ ፫ - ፳፰ ማግኘት ይቻላል ። ለ
ምሳሌ በቁጥር ፹ህ ይሁዳ የአንበሳ ደቦ
ል ወይም የአንበሳ ደቦል የሆንክ ይሁዳ
ቢል ሠምና ወርቅ

ለ/ ይሁዳ እንደአንበሳ ደቦል ነህ ወይ
ም እንደ አን[illegible] ደቦል የሆንክ ይሁዳ ቢ
ል የቅኔው [illegible]ንገድ ንዕዕር ነው ። በቁጥ
ር ፱ እንደ አንበሳ ወይም እንደእንስት
አንበሳ አሸመቀ አደባ ፡ ማንስ ቀሰቅ
ሶ ሊያነሣው ይችላል ተብሎ የተነገረ
ውን መጽሐፋዊ ቅኔ የሀገራችን ሊቃው
ንት ሕዝባዊ ወኔ መቀስቀሻ አድርገው
ለመግለጥ ሲፈልጉ ‟አንበሳው ተሰብ
ሮ ገብቷል ከደበጡ
የሚቀሰቅሰው እስኪ ጐበዝ አምጡ”
በማለት በመስንቆ ዜማ ያንጐራጉሩ
ታል ። የቅኔው መንገድ ውስጠ ወይ
ራ መሆኑ ነው።ይኸውም አንበሳ የ
ተባለው የዱር አውሬ ሳይሆን ለሀገሩ
ተዋቂና ተጋዳይ የሆነውን ጦረኛ የ
ሚያመለክት በመሆኑ ነው ።

በቁጥር ፳፩ ንፍታሌም የተፈታ ሚዳቋ
ወይም እንደተፈታች ሚዳቋ ነው ።
በቁጥር ፳፯ - ብንያም ነጣቂ ተኩላ ወይ
ም እንደነጣቂ ተኩላ የሆነ ብንያም ወ
ዘተ የተሠኙትም በዚሁ ዓይነት ሊተ
ነተኑ ይችላሉ ።

፪/ ሰም ለበስ ውስጥ ወይራ የሆነ የ
መርምር ቅኔም አለ፡-

ይህ ዓይነቱ የቅኔ መንገድ የአንድ ዓ
ይነት ድርጊት ምሥጢሩ ወይም ታሪኩ
ቀደም ብሎ ካልታወቀ በቀር ፍቺው የ
ማይገኝ የቅኔ መንገድ ነው ። በቅዱሳት
መጻሕፍት የቅኔ አጻጻፍ ደንብ ግን ፍቺ
ውም ጭምር ከድርጊቱ በፊት ወይም
በኋላ ስለሚገኝ ለአተረጓጐም ችግር አ
ይፈጥርም ።

አስረጅ ‟ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ
ፍችው የልባችሁን ትዕቢትና ዕልኸኛ
ነት ወይም ክፋትን አስወግዱ ማለት ይ
ሆናል ይህን መሠረት በማድረግ አንድ
የቅኔ ደቀ መዝሙር አቡነ ጴጥሮስ የበ
ዓታ ማርያም ሊቀ ሊቃውንት ሆነው በ
ሚሠሩበት ጊዜ የጳውሎስን መልእክታ
ት ትርጉም ካሳተሙ በኋላ የትርጉም መ
ዛባት አለ ተብሎ ሐሜትናንትርከበመፈ
ፈጠሩ ትዝብቱን በመግለጥ እንዲህ ሲ
ል ተቀኝቶላቸዋል ‟ አንተ የጻፍከውን
መጽሐፍ የሚነቀፍ ያልተገረዘ ነው የ
ሆነ ቆላፍ ደግሞም ያልወጣለት የልቡ
ሸንኮፍ”
ትርጉሙም ያልተማረ ልበ ድፍን እንደ
ማለት እንጂ የመገዘርና ያለመገዘርን
ጉዳይ አያመለክትም በተጨማሪም ፡
‟ ከፈሪሳውያንና ከሔሮድስ እርሾ ተ
ጠንቀቁ ፍችው ከግብዝነት ራቁ ማ
ቴ ፲፮ ፣ ፮

‟ ሂዱ ያችን ቀበሮ እንዲህ ብላችሁ
ንገሩዋት ፍችው ያንን ተንኰለኛ ሔሮ
ድስን ማለት ነው ።

‟ በከተሞች ሁሉ የጥርስን ንጣት

ወደ ገፅ ፲፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# በከፋ ክፍለ ሀገር የጊሚራ (የቤንቾ) ብሔረሰብ

የከፋ ክፍለ ሀገር በስድስት አውራጃዎች የሚከፈል ለም ለም ሀገር ነው ። ታዋቂ ከሆነበትም ግንባር ቀደም ምርት ዋናው ቡና ነው ።

በከፋ የቡናው ምርት ጠንቅቀው በመትከል ከሚመረተው ሌላ በየደኑ ወፍ ዘራሽ በብዛት ይገኛል ከፋ በሌሎችም አዝርእት የታወቀች ናት ። በደኖችዋ ውስጥ ልዩ ልዩ የዱር አራዊት ይገኛሉ ። በክፍለ ሀገሩ ውስጥ ከሚገኙት ከፋ ማጂ ፡ ጅማ ኩሎና ሊሙ ከሚባሉት አውራጃዎች ስድስተኛዋ በሆነችው በጊሚራ አውራጃ ከሚገኘው ከጊሚራ ወይም ከቤንቾ ብሔረሰብ ጋር እናስተዋውቃችኋለን ። የጊሚራ አውራጃ በተፈጥሮ ልምላሜ የተደነቀ ልዩ ልዩ የእህል ዓይነቶችና ፍራፍሬዎች እንደዚሁም ዝንጅብል ኮረሪማና እርድን የመሳሰሉ የቅመም ዘሮች የሚመረቱበት አውራጃ ነው ። በዚህ አውራጃ ውስጥ የቤንቾ ብቻ ሳይሆን የዳይ ሞና (ቡሮ) የአኝዋክ የሙረሌና የጣማ ብሔረሰቦች ይገኛሉ ። እነርሱም በእርሻ በከብት ርቢና በአደን ይተዳደራሉ ።

የቤንቾ (የጊሚራ) ብሔረሰብ ሥራ ወዳድ እንደመሆኑ በኋላቀር የማምረቻ መሣሪያ እየተረዳ ወንዶችና ሴቶቹ ወጥተው በጋራ ይሠራሉ ። እንግዳ መቀበል ስለሚወዱ ቤት ያፈራውን አቅርበው ያስተግዳሉ ። በብሔረሰቡ ዘንድ ውሸት ስርቆት የተጠሉ ናቸው ይህን ሲያደርግ የተገኘ ግለሰብ በሸንጎ ይቀጣል። ስለሆነም ብሔረሰቡ እምነት ማጉደል ስድብ ሰርቆትና ውሸት ለነፍስ ግድያ ወንጀል ምክንያቶች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ድርጊቱን በቶሎ ለማክሸፍ ጥረታቸው ነው ።

ጋብቻን በሚመለከት፣ የቤንቾ ብሔረሰብ አባላትም ጋብቻቸውን የሚፈጽሙት በሽማግሌዎች አማካይነት በጥሎሽ ክፍያ ነው ወጣቱ ለሚፈልጋት ልጃገረድ በወላጆቹ አማካይነት ሽማግሌዎች ተመርጠው ለልጂቱ ወላጆች ይላካሉ ። ከዚያም ለጋብቻው ቀጠሮ ይያዛል በቀጠሮውም ቀን የቀንድ ከብት በጉዦች ተቆጥረው ገንዘብም ታክሎበት ለልጂቱ ጥሎሽ ይከፈላል ። የሚገርመው ነገር ከዚህ ሌላ የማምረቻ መሣሪያ የሆነ አንድ መቆፈሪያም አብሮ ይሰጣል ። ከጋብቻው በኋላ ሚስት ልጅ ሳትወልድ ብትሞት የተጠቀሰው የጥሎሽ ዓይነት ተቆጥሮ ለባል ይመለሳል ። ዳሩ ግን ወልዳ እንደሆን ሴት ከሆነች ጥሎሹ በሙሉ አይመለስም ። የተወለደው ልጅ ወንድ እንደሆን ሴት ከሆነች ጥሎሹ በሙሉ አይመለስም። የተወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ ከጥሎሹ ከፊሉ ይመለሳል በብሔረሰቦች ዘንድ እንደቆየው አጉል ባህልና እምነት ሁሉ አንድ የቤንቾ ብሔረሰብ አባወራ ባለቤቱ የወር አበባዋ ሲመጣ ከዋናው ቤተሰብ መጥታ በተለይ በተሰራ ጎጆ ውስጥ ትሰነብታለች ሰው አይጠይቃትም ምግብ አቀባዩም ሰጥቶ ብቻ ዞር ማለት ነው። በወሊድም ረገድ ሴት ልጅ ከወለደች ለ?ለት ወራት ወንድ ከወለደች ግን ለአንድ ወር በገለልተኛ ጎጆ ውስጥ ትቆያለች ።

በቤንቾ ብሔረሰብ ዘንድ ሰው ሲሞት ሟቹ ታዋቂ ከሆነ ልብሱና የመታሰቢያ እቃው ተይዞ ከበሮ እየተመታ ጦር እየተሰበቀ ጋሻ ለጋሻ እየተጋጩ ልቅሶ ይካሄዳል። ልቅሶውም በአንድ ቀን የማያበቃ ሳይሆን ለብዙ ቀናት ይቀጥላል ። ባለው አጉል እምነት የሟቹ ቤት ንብረት እንደገፈ ስለሚቆጠር ይሰባበራል ይቃጠላል የጓሮ አትክልት ሳይቀር ይወድማል። ቁም ከብቱም ታርዶ ለለቀስተኞች ግብዣ ይውላል ። ይህን ከመሰለው ጥፋት ያመለጠ ሀብት ንብረት ወይም ከብት ከተገኘ ለቀልቻ ይሰጥ ነበር በዚህ ዓይነት የሟቹ ቤተሰብ አግኝቶ ያጣ ስለሚሆን የሚጠብቀው ችግር ነው ።

በቤንቾ (በጊሚራ) ብሔረሰብ መልካም ባህል ጎን የሚታየው አድሃሪ ባህል በባህል ዘመቻው ሳቢያ እንዲወገድ በማድረግ በኩል የተጠናከረ ቅስቀሳና ትምህርት እየተሰጠ ነው ። ለብዙ ጊዜ ወጣቶችን ያሰቃይ የነበረው የጥሎሽ ሸክም ዛሬ ተቃሏል ። የቤት ሃላፊው በሞተ ጊዜ ቤቱ እቃውና ከብቱ አትክልቱ ሁሉ ይወድም የነበረው ቀርቶ ቤተሰቡ እንዲገለገሉበት ሲደረግ ምንም ዓይነት የቁጣ መንፈስ ያልሰፈረበት ለመሆኑ ትምህርት ተሰጥቷል ።

ለወትሮው በልምላሜውና በሚሰጠው የሰብል ዓይነት ሳይታወቅ ብሔረሰቡም የሥልጣኔ ጭላንጭል ሳያይ የቆየው የጊሚራ አውራጃ ዛሬ ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ የሚካሄድበት ሥፍራ ሁኗል ይህም ተጨቁነው ለነበሩ ብሔረሰቦች የሚሻሻሉበትን ጐዳና እየከፈተ ነው ። የመሠረተ ትምህርቱ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተቋቁመው ወጣት ሽማግሌው ትምህርትን በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ ። አሁን ባለው የተባበረ ጥረት የጊሚራ አውራጃ ብሔረሰቦች በቅርብ ጊዜ ጨርሰው ከአድሃሪ ባህል ተላቀው ጠቃሚውን ባህል እንደሚያጐለምሱ የማይጠረጠር ነው ።

<u>በባሌ ክፍለ ሃገር የኤረር ባሬ ብሔረሰብ</u> በባሌ ክፍለ ሀገር ከሚገኙ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች አንደኛው የኤረር ባሬ ብሔረሰብ ነው ። የዚህ ብሔረሰብ አባላት እስከ አብዮታችን ፍንዳታ ድረስ እንደ ማንኛቸውም ጎዳጣን ብሔረሰቦች ተገፍተው የቆዩ ናቸው ። ኑሮአቸውም በታወቀው የዋቢ ሸበሌ ዳርቻና ሸለቆ ሲሆን በመጠኑም ቢሆን በእርሻና በከብት ርቢ ይተዳደራሉ ። በወንዙ ዳር ኑሮአቸው ጊዜያዊ የሆነ ይመስል ጎጆዎቻቸው ከጥቂት ቋሚዎችና ጭራሮዎች የተሰሩ ናቸው ።

ኤረር ባሬዎች ቁመናቸው መልካም በአለባበሳቸው እንደ አካባቢው የአየር ሙቀት ሽርጥና አልፎ አልፎም ጥምጥም ያደርጋሉ ። አቅራቢያቸው የሆኑ ብሔረሰቦች ሱማሌዎችና ዲጊኒዎች ናቸው። ይህ ብሔረሰብ እንደአቅሙ በእርሻ ሲተዳደር ቆይቷል ብንልም የማምረቻ መሣሪያው ኋላቀር ነው መሣሪያዎቹም ከሸክላ ፣ ከእንጨት ከአጥንትና ከድንጋይ የተበጁ ናቸው ። ለመኝታቸው እንደምንጣፍ የሚገለገሉት በሰሌንና በቁርበት ሲሆን ለመቀመጫም በቆዳ ይገለገላሉ ። የብሔረሰቡ አባላት የሚኖሩባቸው አካባቢዎች እምብዛም ለዝናም የታደሉ ባለመሆናቸው በዋቢ ውሃ በመጠቀም ሰብላቸውን ያጠጣሉ በተለይ ዋናው ሰብል በቆሎ ሲሆን በሹል እንጨት ማሳውን እየወጋጉ የበቆሎውን ፍሬ እዚያ ከተው አፈር ይመልሱበታል በቆሎው በእሸቱም ሆነ መከሩ ቤት ከደረሰም በኋላ ዋና ምግብ ይሆናል ። ሌላው የኤረር ባሬ ብሔረሰብ ምግብ አሣ ነው ። ኤረሮች ዓሣን በመረብ አያጠምዱም የራሳቸው የሆነ ማጥመጃ አላቸው ። ቁሳቁሱም ቀፎ የመሰለ ቅርጫት ሁኖ አሣው ወደ ውስጥ ከገባ በኋላ እንዳያስወጣው አፉ ጠባብ ነው ። ይህ የማጥመጃ ቅርጫት ወደ ወንዝ ከመጣሉ በፊት የሸተተ ሥጋ በውስጡ ይደረግና ከወንዙ ውስጥ ሰጥሞ እንዳይቀር በረጅም ገመድ ከግንድ ጋር ያገናኙትና ወደ ወንዙ ይልኩታል ። እዚያም ይቆያል።ሲመለሱ ዓሦች በቅርጫቱ ውስጥ የተደረገውን ሥጋ ሊበሉ ሲጋፉ በቅርጫቱ ሞልተው ይገኛሉ ዓሣ አጥማጁ ያንን ከጐረቤቶቹ ጋር ተሸክሞ ቤቱ ይሄዳል ።

በጋብቻ ረገድ አባወራው በቂ ሰብል ካለው እስከ አምስት ሚስቶች ሊያገባና ሊያስቀምጥ ይችላል ። ሴቶቹ እርስ በርስ አይቀናኑም ዱላ ሲነሳም ሚስት ዝም ብላ አትመታም እርሷም ትበቀለዋለች ። ጐረምሳውና ኮረዳዋ የሚጋቡት በሽማግሎች ጠያቂነት ነው ። የልጅትዋ ወላጆች ጥያቄውን ከተቀበሉ ለልጅትዋ ጥሎሽ አሥራ አምስት ቁም ከብት ያምጣ ይላሉ ። ዓቅሙ ከቻለ ይሰጣል ካልቻለ ቅናሽ ይጠይቃል ከተስማሙ ልጃቸውን ይሰጣሉ እምቢ ሊሉም ይችላሉ ። በኤረር ባሬ ብሔረሰብ የጠለፋ ጋብቻ አለ ። ሀብት ካጣ ከዚህ አይመለስም አማራጩ ይህ ነው ማለት ነው ። ኋላም ያለውን እጅ መንሻ በሽማግሎች አሲዞ እንዲያማልዱት ወደ ልጂቱ ቤት ይልካቸውና እንደምንም እርቅ ይሆንና ጋብቻው በይፋ ይፈጸማል ።

## መልአከ ገነት ጽጌ...

ከገጽ ፤ የዞረ

ረነቱ ሥራ ላይ ቆዩ ።

ሊቁ ጻድቃን ሰማዕታት አያማልዱም የሚል ተከራካሪ አጋጥሟቸው ለፍርድ በቀረቡበት ወቅት ቀጥሎ በተመለተው ጥንታዊ የሙግት ስልት ተከራክረዋል ።

የሊቁ ጥያቄ አባቶቻችን ሐዋርያት የተቀበሉትን መጽሐፍ ትቀበለኛለህን? የተከራካሪው መልስ አባቶቼ ሐዋርያት የተቀበሉትን ሁሉ እቀበላለሁ ጥያቄ ማን ይሙት ?

መልስ ፣ ንጉሥ ይሙት

ጥያቄ ሐዋርያት የተቀበሉት መጽሐፈ ሄኖክ ጻድቃን ና ሰማዕታት በሞት ከተለዩ በኋላ ስለሰው እንዲያማልዱ ሲያስረዳ ጻድቃን ይስእሉ ወያስተበቁዑ ወይጼልዩ በእንተ ውሉደ ሰብእ ፣ ወጽድቅ ከመ ማይ ይውኀዝ በቅድሜሆሙ (ጻድቃን ስለሰዎች ልጆች ይለምናሉ ፣ ያማልዳሉ ፣ ይጸልያሉ ፣ ጽድቅም በፊታቸው እንደውሃ ይፈሳል" እንዲሁም ሕያዋን ይሰዕሉ በእንተ ሙታን ፣ ወሙታን ይሰእሉ በእንተ ሕያዋን (ሕያዋን ስለሙታን ይለምናሉ ፣ ሙታንም ስለሕያዋን ይለምናሉ ብሏል ።

መልስ አዎን ሄኖክ ይኸንን ያሉትን ይናገራል ።

ጥያቄ ከላይ በጥያቄው መነሻ እንዳሳመንኩህ ሁሉ ሐዋርያት የተቀበሉትን የምትቀበለኝ ከሆነ ሐዋርያው በመልእክቱ ፤ ወከመ ከዋክብት ጽልሙታን ወይጸንሐሙ ኩነኔ በከመ ተነበየ ሄኖክ በእንቲአሆሙ ዘውእቱ ሳብዕ እምአዳም ናሁ ይመጽእ እግዚአብሔር በአዕላፊሁ ቅዱሳን መላእክት ወይፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ (ብርሃን እንደሌላቸው ከዋክብት ናቸው፤ ለዘለዓለም የሚሆን ጽኑ ጨለማ ፍርድ ይጠብቃቸዋል ከአዳም ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ እነሆ እግዚአብሔር ፍርድን ያደርግ ዘንድ ብዙ ከሆኑ ቅዱሳን መላእክት ጋራ ይመጣል ፣ ለሁሉም እንደሥራው ፍዳውን ይሰጠዋል በማማለት ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉትን ቢጽ ሐሣውያንን በሚወቅስበት ጊዜ ቃሉን ጠቅሶት ይገኛል ይሁዳ ምዕ 1 ቁጥር 14 - 15 መጽሐፈ ሄኖክ ምዕ. 1 ቁጥር 9 በታተመው።

ስለዚህ ሐዋርያት የተቀበሉትን የምትቀበል መሆንህን ካረጋገጥክ ከሐዋርያት አንዱ የሄኖክን ቃል ተቀብሎ እነሆ በመልእክት ካስተላለፈው መልእክቱም የጻድቃንና የሰማዕታትን አማላጅነት በጉልህ የሚያስረዳ ከሆነ የቅዱሳን አማላጅነት ተቀብለህ እነሆ ተረታልኝ ሲሉ አጠቃላይ የሆነ የፍርድ አሳብ አቀረቡ ።

በፍርዱም የአሸናፊነትን ዕድል ሲቀዳጁ ተቃዋሚያቸው ተረታ ሁለተኛ ደግሞ ሌላ ድንገተኛ ጥያቄ ቀርቦላቸው ሊቁ አጥጋቢ መልስ ሰጥተዋል ።

ጥያቄ ፤ በዘመነ ጽጌ በየሣምንቱ እሑድ ሊቃውንት መዘምራን ከምሽቱ በሦስት ሰዓት ደወል ደውለው በከበሮ በጸናጽል በጭብጨባና በልዕልታ በታላቅ ደስታ ያነጋሉ ወርኃ ጽጌ ግን እመቤታችን ልጅዋን ክርስቶስን አዝላ በምድረ ግብፅ በረሃ ለበረሃ በውሀ ጥም በስደት የተንከራተተችበት የመከራ ወቅት ነው ይህ ለምን ይሆናል ማለት መከራው ስለምን በደስታ ተለወጠ?

ወይ. ገፅ ፳፱ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

~•~•~

**ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፤ ለችግራቸው መፍትሔ የ .ሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።**



**አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ**
**ስልክ ቍጥር 11-66-16**
**የፖ.ሣ.ቁ. 31-37**
**አዲስ አበባ**

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋርያዊ ድርጅት
የምን እንርዳዎ ዓምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ የእግዚአብሔር ረድኤት እንዳይለያችሁ ምኞቴ ነው ።

ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስለ አቀረብኩ መልሱን በናፍቆት እጠባበቃለሁ ።

፩ በሥዕሉ አቋም እንደምንመለከተው ቅዱስ ሚካኤል በቀኝ እጁ ሰይፍ ይዞ ይታያል ፤ ሰይፉንም ቃጥቶታል ። የቃጣው ለማን ነው? በግራ እጁስ ያንጠለጠለው የወርቅ ሚዛን ምን መመዘኛ ነው?

፪ የቤተ ክርስቲያን አስቀዳሾች ቅዳሴ ከተፈጠመ በኋላ የቅዳሴ ጠበል በሚተበሉበት ጊዜ አንዳንዱ ለመድኀኒት ሲጠጣው አንዳንዱ ሰው ለጥም ይጠጣዋል ። ጠበል ራሱ ማየ ገቦ አይደለምን? እናንተስ ምን ሀሳብ ትሰጡኛላችሁ?

፫ የዲያቆን ማዕረግ በብዙዎች ዘንድ በንቀት ዓይን ለምን ይታያል? አብራሩልኝ

፬ኛ አንዳንድ ምዕመናን በቅዳሴ ሥርዓት ስገዱ ለእግዚአብሔር በፍርሀት በሚባልበት ጊዜ ማለት እንማልዳለን ሲባል አንዳንድ ምዕመናን ከመስገድ ይልቅ ከፍተኛ ወሬአቸውን ይቀጥላሉ ለምን?

፭ኛ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ከምሥራቅ መጡ ይላል።የየት አገር ሰዎች ናቸው?

፮ ጌታችን መድኀኒታችን በተወለደ በስንት ቀን ወደ ግብፅ ተሰደደ መልሱን እጠባበቃለሁ ።

ዲያቆን ዘካርያስ ፈይሳ
ከደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን
አዲስ አበባ

**ዲያቆን ዘካርያስ ፈይሳ ጥያቄህን ተመልክተነዋል ።**

**፩ኛው ጥያቄህ** በቅዱስ ሚካኤልእጅስለ አሉት ሰይፍና ሚዛን ነው ። በቅዱስ ሚካኤል እጅ የሚገኘው ሰይፍና ሚዛን መሳል የተጀመረው በመካከለኛው የክርስትና ዘመን ነው በመካከለኛው የክርስትና ዘመን ቅዱስ ሚካኤል በክርስቲያን የሥዕል ጥበብ ፩ኛ አበባና ሰይፍ ፪ኛ ጌታ የተወጋበትን ጦርና ሐሞት የጠጣበትን ዘንግ፣ እንዲሁ ሰይፍ፫ኛ ሚዛንና ሰይፍ እንደያዘ መሳል ተጀምሮአል ይህም የሚያመለክተው አበባ የእግዚአብሔርን ምህረት ሲሆን ቅዱስ ሚካኤል የእግዚአብሔርን ምህረት ይዞ ወደ ሰዎች የሚላክ ፣ የእግዚአብሔርን ምህረት ለሰዎች የሚያደርስ መሆኑን ነው ሰፍነግና ጦር የክርስቶስን መከራ ሲያስታውስ ሚዛንና ሰይፍ የእግዚአብሔርን ትክክለኛና ቁርጠኛ ፍርድ ያመለክታል ።

እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በሰይጣን አንገት ላይ ቅዱስ ሚካኤል እንደተረገጠቁሞ ተስሎ ይታያል ወደማን ነው የሰነዘረው ላልከው ወደ ዲያብሎስ ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን የሚያረጋግጥ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ይላል ። “ በሰማይ ሰልፍ ሆነ ። ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ዲያብሎስን ተዋጉ ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ።አልቻላቸውምም ። ከዚያም ወዲህ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም ። ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው ዲያቢሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ።መላእክቱም ከእርሱጋር ተጣሉ ራዕይ ፲፪፥፯-፲ ይላል ከዚህ የተነሳ የዲያብሎስን ድል መሆን ፤ የቅዱስ ሚካኤልን ድል ማድረግ ለማመልከት ሲባል የተሳለ ነው ።

በግራ እጁ የያዘው ወርቃዊ ሚዛን ደግሞ ከ፦ነያሉ እግዚአብሔር ለዓለም የሚሰጠውን የእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ መላእክት ለዓለሙ የሚያደርሱ መሆናቸውን ከማረጋገጡም በላይ በእግዚአብሔር ዘንድ እውነተኛና ትክክለኛ ፍርድ ለዘለዓለም ፀንቶ የሚኖርና ዓለምም እውነተኛና ትክክለኛ ፍርድ እንዲፈርድ የሚጋብዝ መሆኑን ያመለክታል።ከዚህ ሌላ የሚታዩት ሥዕሎች ግን በየታሪኩ አንፃር ታሪኩን በሚመለከት ሁኔታ ተሥሎ ይታያል ።

ለምሳሌ ግብፃውያን በባህረ ኤርትራ ከፈርኦን ጋር ሰጥመው ሲታዩ ቅዱስ ሚካኤል ደግሞ በእስራኤል ላይ አንገቦ በምህረት ሲያድናቸው ይታያል ። ሌላውም እንዲሁ እንደየታሪኩ ተሥሎ ይገኛል ።

፪ኛው ጥያቄ ስለቅዳሴ ጠበል ጉዳይ ነው

የቅዳሴ ጠበል የሚጠጡ ሰዎች ለመድኃኒትነት እንጂ ለጥም የሚጠጡ የሉም ፣የቅዳሴ ጠበል ማይ ጽሉይ ጸሎተ ቅዳሴ የተፈጸመለት በመሆኑ ለፈውስ የሚሆን ነው ። በመሠረቱ አንድ ሰው ድኅነተ ሥጋ ወነፍስ አገኛለሁ ብሎ ጦሙን ውሎ ቅዳሴውን በሥርዓት አስቀድሶ ከጨረሰ በኋላ በጎፍኑ ወይም በመቁረርት የቅዳሴ ጠበል የሚቀምሰው ለፈውስ እንጂ ለጥም አይደለም ፣ ደግሞስ የቅዳሴ ጠበል የሚቀምሰው ሰው ለጥም ወይም ለመድኃኒትነት የሚጠጣው መሆኑን አንተ በምን አወቅከው? ይህንን ልትረዳ አትችልም ። ምክንያቱም ውሀ ጠምቶኛል ስጠኝ ብሎ ሊጠይቅህ የሚችል ስለማይመስል ነው ስለ ዚህ የቅዳሴ ጠበልን ለጡሃ ጥም የሚጠቀምበት አለ ብሎ መገመት እንደ ስህተት ስለሚቆጠር በዚህ ነገር ባትጠራጠር መልካም ነው ።

፫ኛው ጥያቄ ስለዲያቆናት ማዕረግ ጉዳይ ነው ።

የዲቁና ማዕረግ የሚናቅ ወይም በዝቅተኛ የሚታይ አይደለም ። በቤተ ክርስቲያን ትልቁና ከፍተኛው ማዕረግ ዲቁናና ቅስና ነው ። በቤተ ክርስቲያናችን የሚያጠምቁ ፣የሚያቆርቡ ዲያቆናትና ቀሳውስት ሲሆኑ ዲያቆናትንና ቀሳውስትን መናቅ ግን የቤተ ክርስቲያንን ማዕርግ እንደመናቅ ይቆጠራል ።

ከሁሉ የሚያስገርመው ግን ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተማሩት ታላላቅ ሊቃውንት ሳይቀር የዲቁናንና የቅስናን ሥራ መናቃቸው ነው ። በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የተማሩ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ብዙ ናቸው ባይባልም በመጠኑ አሉ ።

ይሁን እንጂ ትምህርታቸውና ዓላማቸው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሆኖ ሳለ በቅስናና በዲቁና ተሰማርተው ሲያገለግሉ አይታዩም ። በቅስናና በዲቁና ማገልገልንም እንደውርደት ይቆጥሩታል ። አብዛኛዎቹ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እየናቁ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን መፈለጋቸው ሳያስገርም አይቀርም ። መቼም የዲቁናንና የቅስናን ማዕርግ ዝቅ ሊያደርገው የቻለው አንዱ የዲያቆናቱና የቀሳውስቱ ድካም ጭምር መሆኑ አይካድም ። ምክንያቱም በዲቁናና በቅስና የሚያገለግሉት ሰዎች በትምህርቱ ስለማይገፉበት ፣ በጅምር ስለሚተውት ዲያቆን ወይም ቄስ ሲባል ሊቃውንቱ የሚያፍሩበትም ክንያትም ይኸው ነው።ዳሩ ግንዲያቆን ወይም ቄስ መሆን የሚገባው “ወኢይኩን አሑዱሂ ቀሲስ ዘኢየአምር ነገር መጻሕፍት አምላካውያት ሠናያት ወፈጽፉደሰ አርባዕተ ወንጌላተ መልካም የሆነ የአምላክን ነገር የሚናገሩ መጻሕፍትን ይልቁንም አራቱን ወንጌላት ያላወቀ አንዱ እንኳን ቄስ አይሁን” ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 6.212 በተባለው መሠረት በትምህርቱ ከሁሉ በላይ የሆነ የሚያነበውን የሚተረጉም ፣ ምዕመናንን የሚያስተዳድር መሆን ሲገባው ለዲቁና ወይም ለቅስና ሥራ የሚመረጡት ወይም ይህንን ሥራ የሚይዙት ለመተዳደሪያያሀል ከሆነየዲቁናንማዕረግምበንቀትዓይንእንዲታይ የሚያደርገው ምክንያትም ይኸው ሊሆን ይችላል ።

ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ደረጃ ያለው የዲቁናና የቅስና ማዕርግ ክብሩ እንዲጠበቅ በዚህ ሥራ የሚሠማሩ ሁሉ ነገረ መለኮትን አብራርተው የማስረዳት ፣ መጻሕፍትን ተርጉመው የማስተማር ችሎታ ያላቸው ሊቃውንት ዲያቆናትና ቀሳውስት ሆነው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም ማገልገል አለባቸው ። ምንአልባት ምሁራኑ ባለዲግሪውም ዲያቆን በዲቁናና በቅስና ሥራ ቢሠማሩ በሌላው ሥራ ተሰማርተው የሚከፈላቸውን ደመወዝ አያገኙም የሚል አስተያየት ይኖር ይሆናል ።

ይህ እንዳይሆን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጉዳዩ ካሰቡበት በሌላው ቦታ እየሠራ የሚያገኘውን ደመወዝ በቅዳሴ ሥራ የተሠማራው ባለዲግሪ ዲያቆን እንዲያገኝ ቢደረግ የዲቁና ማዕርግ በንቀት ከመታየት ይልቅ በክብር ይታያልና ቢታሰብበት መልካም ነው ። በተረፈ የዲቁናን ሥራ “ባጣ ቆየኝ” በማድረግ የሌላ ሥራ መፈለጊያና የትምህርት መማሪያ ለማድረግ ብቻ ከሆነ የዲቁና ማዕርግ አንተ እንዳልከው በንቀት ከመታየት አይድንም ።

ሊቃውንቱም የዲቁናና የቅስና ማዕርግ ከሌላቸው ሕዝባውያን እንጂ ካህናት ስላይደሉ እነርሱም ቢሆኑ የዲቁናንና የቅስናን ሥራ መናቅ አይገባቸውም

4ኛ አንዳንድ ምዕመናን በቅዳሴ መካከል ስገዱ ሲባል ተቀምጠው እንደሚያወሩ ተጠይቋል

ይህ ተግባር በየቤተ ክርስቲያኑ በብዙ ሰዎች ሲፈጸም የሚታይ በመሆኑ የሚያሳዝን ጉድለት ነው ከመቀመጣቸው ደግሞ የደራ ወሬ በመያዝ ሌሎቹ በሰቂለ ህሊና የሚጸልዩትን ግራ ሲያጋቡና ሲያበሳጩ መታየቱ በጣም ቅር የሚያሰኝ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ጉዳይ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና የወንጌል መምህራን ሊያስቡበት የሚገባ ጉዳይ ነው ።

በቅዳሴ መካከል እንኳን ወሬና የግል ጸሎት መያዝም የተከለከለ በመሆኑ ምዕመናን በአንድ ልብ ሆነው ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የአንድነት ጸሎት ስለሆነ የግል ጸሎት አይፈቀድም በማኅበር ጸሎት ወይም በቅዳሴ ጊዜ የግል ጸሎት የሚይዝ ቢኖር ስህተተኛ በማኅበር ጸሎትም የማያምን በመሆኑ በቅዳሴ ጊዜ ባይገኝ ይሻለዋል ።

5ኛ ጥያቄ ደግሞ በክርስቶስ ልደት ጊዜ ከምስራቅ መጡ ስለተባሉት ሰዎች ነው

ሰብአ ሰገል ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መጥተው የሰገዱለት ቀድሞ በባቢሎንና ፋርስ ዛሬ ኢራቅና ኢራን ከሚባሉት አገሮች ሲሆን በአጠቃላይም አረቢያ ይባላል ።

ስለ6ኛው ጥያቄ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰደደው በተወለደ በሁለት ዓመቱ ነው

ወደ ገፅ ፳፬ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ቅርሶች አሳዛኝነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት እንደመሆንዋ በጥንታውያን የብራና መጻሕፍት ፣ ከወርቅ ፣ ከብር ፣ ከብረታ ብረትና ከዕፅ በተቀረጹ ቅርጻ ቅርጽና መስቀላት ፣ በወርቅና በብር ሰገጥ በተዋቡ አልባሳት የበለጸገች የቅርስ ባለቤት ነበረች ። ይሁን እንጂ ለቅርሶችዋ የሚደረገው ጥንቃቄ እስከዚህም ስላልሆነ አብዛኞቹ ታላላቅ ቅርሶች በልዩ ልዩ ምክንያት ታጥተዋል ። እንዲሁም በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በፍሳሽ ርሰው በብል ፣ በአይጥና በሌሊት ወፍ ተቆነጻጽለውና በሌላም አደጋ ተጐድተው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑትን ቅርሳቅርስና ንዋያተ ቅድሳት ሁኔታ ማየት እውነተኞች ኢትዮጵያውያንን እጅግ ያሳዝናል ።

አሁን በአሳዛኝ ሁኔታ ላይ ከሚገኙት አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ቅርሳ ቅርስና ንዋያተ ቅድሳት በተቀዳሚ ሊጠቀስ የሚገባው የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ሁኔታ ነው ። የቀጨኔ ደብረሰላም መድኃኔ ዓለም ከተመሠረተ የሰባ ዓመታት ዕድሜ አለው ። ቤተ ክርስቲያኑ በነዚህ ዓመታት በርከት ያሉ ቅርሳቅርስና ንዋያተ ቅድሳት ባለቤት ሳይሆን አልቀረም ነበር ። ግን አሁን ብዙዎቹ ቅርሳ ቅርስ የውሃ ሽታ ሆነው የቀሩ ይመስላል ቅርጻቸው ሊጠፋ የተቃረበና አሳዛኝ የሆነ ጉዳት የደረሰባቸው ቅርሳቅርስና ንዋያተ ቅድሳትም ለምስክርነት አሉ ። ከግድየለሽነትና ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ በቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ዕቃ ቤት ውስጥ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው

ንዋያተ ቅድሳት

፩ኛ የወርቅ ካባዎች ፳፫
፪ኛ የወርቅ ለምዶች ፫
፫ በወርቅ ሙካሽ የተሠሩ አብደላ ከኒ ቀሚሶች ፪
፬ የወርቅ ቀሚሶች ፲



የቀጨኔ መድኃኒዓለም ሰበካ ጉባኤ ም ሊቀመንበር ንዋያተ ቅድሳቱን ለት ንሣኤ ዝግጅት ክፍል ባስጎበኙበት ወቅት

፭ ወርቀ - ዘቦ ላንቃ ካባዎች ፲፩
፮ የብር ለምድ ፩
፯ በሙካሽ የተሠሩ የወርቅ ለምዶች ፫
፰ የጥሩ ሐር ካባዎች ፲፰
፱ ሁለተኛ ደረጃ አብደላ ከኒ ቀሚሶች ፳
፲ ሁለተኛ ደረጃ ሐር ቀሚሶች ፲፪
፲፩ ሁለተኛ ደረጃ ለምዶች ፱
፲፪ ከፋይ ቀሚስ ከወርቅ የተሠራ ፩
፲፫ የተለያየ መልክ ያላቸው የመቀደሻ ቀሚሶች ፳፭
፲፬ በወርቅ ሙካሽ የተሠሩ መጐናጸፊያዎች ፭
፲፭ መጋረጃዎች ፱
፲፮ ጥንግ ድርብ ፩
፲፯ በሙካሽ የተሠሩ ልዩ ልዩ ቀሚሶች ፯
፲፰ የወርቅ ጥላዎች ፫
፲፱ በሙካሽ የተሠሩ የብርና የወርቅ ጥላዎች ፳፰
፳ ሁለተኛ ደረጃ ጥላዎች ፭
፳፩ ሦስተኛ ደረጃ ጥላዎች ፴፯
፳፪ ቀጸላ በሙካሽ የተሠራ ፩
፳፫ ቀጸላ ወርቀ ዘቦ ፩ በድምሩ ፪፻፶፰ (ሁለት መቶ ሃምሳ ስምንት) ያህል ቅርሳ ቅርስና ንዋያተ ቅድሳት በብልና በአይጥ ተበልተው አመድ ሆነዋል ። እነዚህ ለምስክርነት ቅሪታቸው ያልጠፋ ስለሆነ ተገኝተዋል እንጂ በልዩ ልዩ ምክንያት ቅሪታቸው የጠፋ ቅርሶች እንደሚኖሩ ይገመታል ።



እነዚህ ከወርቅና ከብር የተሠሩ ቅርሶችና ንዋያተ ቅድሳት እንዲህ ሊጐዱና ከጥቅም ውጭ ሊሆኑ የበቁት ዕቃ ቤቱ ለሃምሳ ዓመታት ያህል ያለ ታዛቢ በአንድ ሰው እጅ ብቻ ተይዞ ስለቆየ ነው ተብሎአል ። ቤተ ክርስቲያኑ ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ እስከ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም. ድረስ የቤተ ክርስቲያኑን መጻሕፍት አልባሳትና ንዋያተ ቅድሳት ቁጥር የሚያሳይ መዝገብ አልተገኘም ። ቤተ ክርስቲያኑ ከተመሠረተበትና አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ መዝገብ ቤ.ዘጋጅለትና ንዋያተ ቅድሳቱ ቢመዘገቡ ፡ ከዚህም ጋር የዕቃ ቤቱ ኃላፊነት በአንድ ሰው ብቻ ለሃምሳ ዓመታት ያህል ተይዞ እንዲቆይ ከማድረግ ይልቅ በሁለት ወይም በሦስት ዓመት የዕቃ ቤት ሹም ለውጥና የንዋያተ ቅድሳት ርክክብ ቢደረግ ኑሮ ይህን ያህል የቅርስና የንዋየ ቅድሳት መባከን ባልደረሰም ነበር ።



አሳዛኝ ብል ሽት ከደረሰባቸው የቀጨኔ መድኃኒዓለም የወርቅ ካባዎች ለምዶችና ቀሚሶች በከፊ

ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለጹት ከአያያዝና ከአጠባበቅ ጉድለት የተነሣ ወይም አይጠቅሙም ተብለው በመጣላቸው ጉዳት የደረሰባቸው ግን ቅሪታቸው ፈጽሞ ሳይጠፋ ለምስክርነት የተገኙ ናቸው ። በጥራትም ሆነ በብዛት ከዚህ የሚበልጡ ቅርሶችና ንዋያተ ቅድሳት ሳይባክኑ እንዳልቀሩ ይገመታል ። ከመሠረቱ መዝገብ እንዳይኖር የተደረገውም የሚጠፋውና የሚለማው እንዳይታወቅ ለማድረግ ታስቦ ይመስላል ።

እነዚህም ትልቅ ብልሺት የደረሰባቸው ንዋያተ ቅድሳት በአሁኑ ጊዜ በእግዚቢሽን መልክ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ በሚገኝ አዳራሽ ውስጥ ተዘርግተው እየተጐበኙ ናቸው ። በዚህም አጋጣሚ የአካባቢው ምእመናንና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች በቦታው ተገኝተው ተመልክተውታል ። በጊዜው ያሉ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያኑ ተቆርቋሪዎች ይህን አሳዛኝ ሁኔታ ለሚመለከተው ሁሉ ሲያሳዩ ለትንሣኤ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም አሳይተዋል ። ታዲያ ለዚህ የባከነ ቅርስ ጠያቂው ማን ነው ? ተጠያቂውስ ?

ጥፋቱ በይፋ የታወቀው የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ንዋየ ቅድሳት ብቻ በዚህ እትም ተገለጠ እንጂ በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ይህ አይነቱ የቅርሳ ቅርስና ንዋየ ቅድሳት መባከን ይኖር ይሆናል የየቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች መጻሕፍትንና ንዋየ ቅድሳትን ሁሉ በተገቢው መዝገብ እየመዘገቡ በጥንቃቄ እንዲያዙ የማድረግ ሥራቸውን ባይዘነጉት መልካም ነው ።

በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር የተቋቋመው የቅርሳ ቅርስና ንዋየ ቅድሳት መመሪያም ቅርሶችና ንዋያተ ቅድሳት የማይባክኑበትን ዘዴ እያጠና ለየአብያተ ክርስቲያናት መዛግብት እንዲኖሩአቸው ያልተመዘገቡ መጻሕፍትና ንዋያተ ቅድሳት እንዲመዘገቡ ማድረግ የመምሪያ ቀዋሚ ሥራ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ።



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማት ሥራዎች እንዲስፋፉ የተቋቋሙት እንዲጠናከሩ የመሪዎችዋ እቅድ ነው ።

የልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚቻለው በየመስኩ ተሠማርተው ቀና አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ ካህናቱ በሙያ ትምህርት ሰልጥነው ፣ የወንጌልን ትምህርት ለምእመናን እንዲሰጡ ፣ የልማት ሥራዎችን እንዲሠሩ ፣ የተቋቋሙትን እንዲያጠናክሩ ፣ በአጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያን ሕልውና ፣ ለካህናቱ ዕድገት የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማከናወን ይችሉ ዘንድ ለልማት አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ አስቀድሞ ማሟላት ተገቢ መሆኑንም ያምናሉ ፣ በዚህ ዓላማ መሠረት ከእርዳታ ሰጭ ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ካህናት በቀለምና በሙያ ትምህርት መሰልጠን ከጀመሩ ዘመኑ በአጭሩ የሚገመት አይደለም ።

በመሆኑም በቤተ ክርስቲያንዋ መሪዎች እቅድ የልማት ሥራ እንዲስፋፋ የተጀመረው እንዲጠናከር የጠበቀ ቁጥጥር በመኖሩ አሁንም የሚደረገው ጥረት የሚያኮራና ካህናቱን ለዕውቀት የሚያሰባስብ ነው ።

ለምሳሌ የካህናት ማሰልጠኛዎች በየቦታው መቋቋማቸውና ካህናቱ ለልማትና ለወንጌል ትምህርት የሚያበቃውን የመጀመሪያውን ደረጃ ትምህርት መሳተፋቸው በቂ ምስክር ነው ።

ሆኖም እስከ አሁን እንደታየው በየማሰልጠኛው የሚሰጠው ትምህርት ካህናቱን ለልማት የሚያዘጋጅና የቀሰሙት ትምህርት ወደሌላ የሚተላለፍ ሆኖ አላገኘነውም ። ምክንያቱም እስከአሁን በትምህርቱ ከተሳተፉት ካህናት የቀሰሙትን ትምህርት ለሌላው ማስተላለፍ እንዳልቻሉ እናያለንና ነው ።

፩ኛ/ በካህናት ማሰልጠኛዎች በልማትና ክርስቲናዊ ተራድኦ መምሪያ አማካይነት ፣ ፪ኛ/ በመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ ሰበካ ጉባኤ ዋና መምሪያ በቤተ ክርስቲያናችን ባለሙያዎችን ለማበራከትና የሰበካ ጉባኤን አቅዋም ለማጠናከር በየጊዜው ትምህርታዊና ጥናታዊ ሰሚናሮችን በማዘጋጀት ያሰለጥናል ፣ በዚህም ዝግጅት ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚወጣ እናውቃለን ፤ በዚህም በኩል ጥናቱን የተከታተሉ ካህናት አብዛኛዎቹ ለስብከተ ወንጌል ሲፋጠኑ የሰበካ ጉባኤን አቅዋም ለማጠናከር የሚያደርጉት ጥረት እንደታሰበው ሆኖ አልተገኘም ።

ይህ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያንዋ መሪዎች ጥረትና የካህናቱ ድካም ውጤት አልባ እንደሆን በተመልካቾችና በካህናቱም ዘንድ በጉልህ ይነገራል ።

ስለዚህ ይህን አሠራር አሁን ከሚታየው እንቅስቃሴ እጅግ በጣም ጠንከር ባለ አመራር ለመምራት ይቻል ዘንድ በካህናት ማሰልጠኛዎች ፣ በሰበካ ጉባኤ ዋና መምሪያና በየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት የሚሰጠው ትምህርት በልማት አቅጣጫ ያተኮረ ቋሚና ተጨባጭ የሆነ አቅዋም ቢጣልበት የተሻለና ውጤቱ የሚያኮራ ቋሚ ሥራ ማትረፍ ይችላል ።

በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለው የልማትን መሠረት ለመጣልና የተጀመረውን ለማጠናከር የሚቻለው ሠራተኛው አስቀድሞ በትምህርት መታነጽ እንዳለበት ቢታወቅም እስከአሁን በተግባር እንደታየው ደግሞ ተማሪውን አስተምሮ ወደመጣበት መመለሱ ብቻ ጥቅሙ የማያመዝነው ለተማሪው ቢሆን እንጂ ለቤተ ክርስቲያንዋ የእድገት ምልክትን አላሰየም ።

እንግዲህ በዚህ አሠራር ለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገት ቋሚ መሠረትን ለመጣል የሚያስችሉ አንዳንድ ነጥቦችን እናቀርባለን ።

ለካህናት ማሰልጠኛ ፣ ለሰበካ ጉባኤ ማቋቋሚያና ማጠናከሪያ የሚገኘው የእርዳታ ገንዘብ በልማት አቅጣጫ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ቋሚ መሠረት እንዲጣልበት ቢደረግ በየማሠልጠኛዎቹ እንደየአካባቢው ሁኔታ ቋሚ የገንዘብ ምንጭ የሚያስገኙ የልማት ማመንጫ ሞተሮች ተቋቁመው ካህናቱ በማሰልጠኛዎቹ በሚሰለጥኑበት ወቅት ከሚቋቋሙት ሞተሮች ጋር ልምምድ እንዲያደርጉ ጥናት ቢወሰድ ፤ አሁን አሉ ከሚባሉት ፰ ማሰልጠኛዎች ውስጥ የብረታ ብረት ማቅለጫ መበየጃያና የእንጨት መሰንጠቂያ ሞተሮች እንዲቋቋሙ ቢታሰብበት ፣

በየመንበረ ጵጵስናው የመጽሐፍ ማተሚያ ቤቶች የሚቋቋሙበት መንገድ ቢቀየስ ፣

በየሀገረ ስብከቶችና አመች በሆኑ ቦታዎች ሁሉ የልብስ ተክህኖ ማዘጋጃ የልብስ ስፌት መኪናዎች ፣ የሹራብ መሥሪያ ማሽኖች የዳቦ መጋገሪያ ቤቶች ፣የሻማና የጧፍ ማዘጋጃ መሣሪያዎች ፤ እንዲዘጋጅና ካህናቱ በዚህ ሙያ ልምድ እንዲኖራቸው ቢደረግ ፤

እጅግ በጣም አመች ነው በሚባል በት ቦታ ለዳቦ ዱቄት ማስፈጫ የሚያገለግል የእህል ወፍጮ ቢቋቋም ።

በመንበረ ፓትርያርክ ጠ ጽ ቤት ግቢ እንድየመኪናዎቻችን ሕይውትየሚታደስበት ጋራዥ ቢከፈትና ካህናቱ ወይም የቤተ ክህነት ሠራተኞች በዚህ ሙያ እንዲለማመዱ ቢደረግቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ የልማት ሥራዎችን አዘጋጀች ለማለት ይቻላል ።

ከዚህ ሌላ ካህናቱ የአንጠረኛነት ፣ የቀጥቃጭነትና የሽመና ሥራዎችን ያጠኑ ዘንድ በየማሰልጠኛዎቹ እነዚህ ሁሉ ቢሰበሰቡ ጥናቱን ሊከታተሉት ይችላሉ ብለን እንገምታለን ።

በአጠቃላይ እነዚህንና የመሳሰሉትንም ንድፈ ሃሣቦች በትንተና በማስቀመጥ እንመለከታቸዋለን ።

ለምሳሌ ቅዱሳት መጻሕፍትን ብንጠቅስ ዛሬ በየገዳማቱና አድባራቱ በድርጅቶችና ግለሰቦች እንደመፈለጋቸው መጠን ቤተ ክርስቲያናችን እኒህን የራስዋ የሆኑ መጻሕፍትን በማተም ለፈላጊ ባለማቅረብዋ በፈላጊዎች ዘንድ ከፍተኛ ችግር እንዳለ ይታያል ።

ይህ መሆኑ ከታወቀ ዘንድ የሚመለከቷትን መጻሕፍት በግልዋ አሳትማ በካህናቶችዋ ለማሸጥ እንዲቻል በየሀገረ ስብከቶች መንበረ ጵጵስና ግቢ ውስጥ ማተሚያ ቤቶች እንዲቋቋሙ ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ይሆናል ።

በንዋየ ቅድሳት ረገድ ም ጧፍና ሻማ በቀላሉ የሚሠሩ በመሆናቸው የሻማና የምንጣፍ ሥራም በዚሁ ዓይነት እየተሞከረ በመሆኑ ይዞታው ተጠናቅሮ በየተወሰኑ ቦታዎች ቢቋቋም ምርቱ በቤተ ክርስቲያንዋ አቅራቢነት ለቸርቻሪ እንዲበተን ቢደረግ ካህናቱ በኑሮአቸው ተደስተው የሰበካ ጉባኤ አቅዋምም በቀላሉ ሊጠናከር ይችላል ።

ከጃንጥላ እስከ ልብሰ ተክህኖ በቤተ ክርስቲያን ቁጥጥር እንዲዘጋጅ ቢደረግና ካህናቱ በዚህ ሙያ ልምምድ ቢወስዱ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ እንደሚፈጥር እናምናለን ስለዚህም ለዚህ ሥራ የሚያገለግሉ መኪናዎች ቢዘጋጁና ሥራው እንዲስፋፋ ቢደረግ መልካም ነው ።

ከብረታብረት ፣ ከብርና ከወርቅ የሚሠሩ መስቀል፣ጽዋ፣ጻናጽል ፣ጻሕል ፣ መቋሚያ የመሳሰሉት እስከአሁን በራስዋ ኃላፊነት ያልተዘጋጁ በመሆናቸው በሌሎች ባለሙያዎች በመሠራት ከፍተኛ ገቢ እንደሚያገኙባቸው ስናውቅ ራስዋም ሠርታ ለሌላው መሸጥ ሲገባት ከፍተኛ ገንዘብ እያወጣች ስትገዛ መታየትዋ ለልማት እንቅስቃሴዋ ማዳከሚያ ምክንያት ነው ።

ስለዚህም በካህናት ማሰልጠኛውና በሰበካ ጉባኤ በየሴሚናሩ ከሚወጣው ገንዘብ ይህን ለመሰለው አገልግሎት የሚውልበት ዘዴ ቢፈለግ ቤተ ክርስቲያን ከተረጂነት ወደረጂነት እንደምትሸጋገር እናምናለን ።

ዳቦ መጋገሪያ ዘይት መጭመቂያና የመሳሰሉት በመጠኑም ቢሆን በየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት መጀመራቸውን እናውቃለን ፣ ነገር ግን የታሰበውን ያህል ለማዘጋጀት አንዳንድ ችግሮች ስለሚኖሩ መፍትሔ ቢፈለግላቸው ሊጠናከሩ እንደሚችሉ ግልጽ ነው ፣ ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ችላ ራስዋን በራስዋ ታስተዳድር ከተባለ በዚህ ረገድ ላለው ችግር ማስወገጃ ታላላቅ ወፍጮዎች ቢቋቋሙ ጠቃሚ ይሆናሉ ።

ጋራዥ ቢከፈት መልካም መሆኑን ጠቁመናል ቤተ ክርስቲያናችን በየሀገረ ስብከቱ የሚገኙ መኪናዎችዋ የራስዋ የሆነ የመኪናዎች መጠገኛ ጋራዥ ባለመኖሩና የገንዘብ ችግር በመኖሩ መኪናዎች ተበላሽተው ያለአገልግሎት መቀረጣቸው በጉልህ የሚታወቅ ነው።

ስለዚህ ይህን ችግር ለማቃለልና በአንፃሩም ገቢ ለማስገኘት ይቻል ዘንድ በመንበረ ፓትርያርክ ጠ ጽ ቤት አንድ ጋራዥ ቢከፈት በልማት አቅጣጫ ከፍተኛ ገቢ እንደሚገኝ እናምናለን ።

ከዚህ ሌላ እስከ አሁን በጐፋ ገብርኤል እደጥበብ ማሰልጠኛ ፣ በቤተክህነት እንጨት መሰንጠቂያ ፣ በሰዋስወ ብርሃን ቅ ጳውሎስ የሻማ ፋብሪካ ሥራ ተጀምሮ ጭል ጭል ይሉ ነበር ፣ ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያት እየተዳከሙና አንዳንዶቹም ጨርሰው እንደወደሙ እንረዳለን ።

እነዚህንም ለማጠናከር ከፍተኛ ቁጥጥር ማድረግና ተጠናክረው የገቢ ምንጮቻቸው እንዳይቋረጥ ቢደረግ ይጠቅማል ።

የእንዱስትሪ ባለቤት ለመሆን የበቁ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ የምንሰማው በዚህ አይነት ሠርተው በማሠራቸው ነውና የእኛም ቤተ ክርስቲያን ለቀለም ትምህር ብቻ ከፍተኛ ገንዘብ ከማውጣት ይልቅ እስከአሁን ባሳየነው አስተያየት መሠረት ተጨባጭና የገንዘብ ምንጭ ለሚፈጥሩ ሥራዎችም የገንዘብ ወጭ ቢደረግ መልካም ነው እንላለን ።

በለጠ አበበ

## የድርሰት አጻጻፍ ዘዴ...

ከገፅ ፺ የዞረ

እሰጣለሁ ፍችው በምትኖሩበት ሥፍራ ሁሉ እንጀራ የማጣትን ችግር አመጣባችኋለሁ ማለት ነው ። ይኸውም ጥርስ ካልበሉበትና ካላኘኩበት አለማደፋን ይገልጣል ። አሞፅ ፬፡፮

" የበጎችን መንጋ ከድቶ / በትኖ / ለሸሸ ለማይታመን ዕረኛ

" አሁንስ መጥረቢያ በዛፎች ሥር ተቃጥቶዋል የተሠፉትንም በዚሁ ዓይነት መተንተን ይቻላል ከዚህ ዓይነት የቅኔ መንገድ ብዛት በሽህ የሚቆጠር መሆኑን በጽሞና ማስተዋል ይገባል ። በተለይ ግን ስለሰምና ወርቅ ከፍ ብሎ በኦሪት ዘፍጥረት ፵፱ የገለጥነው ማስረጃ ግልጥ ሆኖ ካልታየ ትክክለኛውን ግልጥ የሆነውን የሠምና ወርቅ ቅኔ ማስረጃ በማቴ ፲፪ ' ፴፭ መመልከት ይቻላል ። እርሱም " መልካም ሰው ከመልካም ልቡ መዝገብ መልካም ነገር ያወጣል የሚል ነው ። ይኸውም ሠናይ ወይም መልካም የሚለው ቃል ቅጽል ሲሆን መዝገብ ሰም ልብ ግን ወርቅ መሆኑን እናስተውል ። ሌሎችን የቅዱሳት መጻሕፍት ቅኔዎች መንገድ በተከታዩ ቁጥር እስክናቀርብ ደህና ቆዩን

ቄስ መክብብ አጥናው





www.ethiopianorthodox.org

# ቅርሳችን ይጠበቅ

አገራችን ኢትዮጵያ በረዥም ጊዜ የነፃነት ታሪኳ የተደነቀችና የባሕል ቅ ቅርሶቿም ከማንኛውም አገር ግልባጭ ያልሆኑ ፤ በራስዋ ሊቃውንት አእምሮ ታስበው የተሠሩ ፤ በስነ-ጥበብ አድና ቂዎች ዘንድ እጅግ የሚያስደንቁ ቅርሶ ች አሏት ።

ይሁን እንጅ ለቅርሳ ቅርስ አጠባበቅ ከፍተኛ ትኩረት ባለመደረጉ በባሕል ሙያ የበለጸጉ ጠበብት ብራና ዳምጠ ው ፤ ቀለም አውጥተው ፤ የመቃ ወይም የሸንበቆ ብር ቀርጸው የጻፏቸው መ ጻሕፍት እንዲሁም የጥበበ ዕድ ምሁራ ንና አንጥረኞች የሠሩአቸው ሐረጋቸው ና ኀብራቸው ታይተው የማይጠገቡ መስቀሎችና ልዩ ልዩ የጌጣ ጌጥ ዕቃ ዎች በታወቁ ሊቃውንት የተሣሉ የሚ ናገሩና ልቡሳነ ሥጋ የመሳሰሉ ሥዕሎ ች ተገቢ ጥበቃ ባለመደረጉ ለአያሌ ዘ መናት በቀላሉ እየተዘረፉ ወደ ውጭ አገር በመሄዳቸው የሌላውን አገር ሙ ዝየም አበልጽገው እናገኛቸዋለን ። ሌላ ቀርቶ የጥጡ መንደፊያ ደጋን ፤ መ ታረሪያውና መቀንጠቢያው እንኳን አ ልቀረም ።

አገራችን ኢትዮጵያ ጐብኞችን የሚ ጋብዙና የሚስቡ አያሌ ነገሮች አሏት ተፈጥሮ ያደላት ለስላሳው አየርዋ ፤ በ አራቱ ማዕዝን የሚፈሱት ወንዞቿ ፤ በ ዓይነትና በቀለም የተለያዩት አዕዋፍና እንስሳት እንዲሁም የመልክዓ ምድር አቀማመጥና የዕፅዋቱ ዓይነት ብዛት ወዘተ... ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከ ፍተኛ ጥናት እየተደረገባቸው ለአገር ብልጽግና ለወገኖች ደኅንነት ማዋል ሲቻል ኅብረተሰብአችን ሳለው ድሃ ሆኖ ለዘመናት ኖሮአል ።

በእርግጥ የቅርሳ ቅርስን ጥቅም የተ ረዱ የውጭ አገር ሰዎች ከአንድ አንድ በፍቅረ ነዋይ ከተበከሉ ምንደኞች ጋር በመመሳጠር ከዘረፉ የተረፉትንም የ ወግና የታሪክ ዕቃዎች የፍልስፍና መጻ ሕፍት ፤ በጠቅላላው ቅርሳ ቅርሶችን አብዛኛዎቹን ዋናውን ወስደው ግልባ ጩን (ፎቶ ኮፒውን) በመተው የቀሩት ን ደግሞ በፎቶ አፍሴት እያነሡ ወደ አ ገራቸው ሙዚየም ፤ ቤተ መጻሕፍትና ዩኒቨርሲቲ በመውሰድ ከአንድ ዐረፍተ ዘመን በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ምን አይከማችሁ የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ከዚህ አለላችሁ ፤ በማለቶ ቱሪስ ቶች ፤ የጥናትና የምርምር ሰዎች ወደ አገራችን እንዳይመጡ ስለሚያደርጉ የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ያላቸ ው ሁሉ አርቀው ሊያስቡበት ይገባል ።

ሌላው ለቅርስ መባከን ምክንያት የሆነው ደግሞ በአዋቂዎች ሳይጠና የ ሥዕል ፤ የአብያተ ክርስቲያናት ሕን ፃና የጥንታውያን መጻሕፍት ጥራዝና ድጉሣት ፤ እድሳት ነው ። በሌላው ዓለ ም አንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም የቅር ስ ዕቃ ከሃምሳ ዓመት ዕድሜ በላይ ከሆ ነው በፈሳሽና በልዩ ልዩ ምክንያት ቅ ርጹን ፤ ውበቱንና ጥንታዊ ቅርስነቱን እንዳያጣ ብርቱ ጥንቃቄ ይደረግለታ ል ። ይህም ማለት ዝናም ገብቶ ሥዕሉ ንና ሐረጉን እንዳያበላሸው ይጠበቃል እንጅ የነበረውን አፍርሶ ወይም አሻ ሽሎ መሥራት የባሕልና ቅርሳ ቅርስ ጠበብት አጥንተው ያስፈልጋል ካላሉ በስተቀር አፍርሶ መሥራት ወይም ጥን ታዊ ይዘቱን በሚያጠፉ ሁኔታ ማደስ ከቶ አይደረግም ። ይህም እንዲሆን የ ሚያስፈልገው አዲሱ ትውልድ የሚፈ ላሰፈውና የሚራቀቀው ፤ ስነ-ጥበብን በአባቶች ፤ በአያቶቹና በቅድመ አያቶ ቹ በተሣሉት ሥዕሎች ፤ ሐረጐችና ቅ ርጸ ቅርጾች ትምህርት ለመቅሰም እን ዲችል ነው ።

በመሠረቱ አንድ ኅብረተ ሰብእ ወ ይም አገር የረዥም ጊዜ ነፃነቱ ምልክ ቶች ወይም የሚታወቀው በባሕሉ ፤ በ ቋንቋው ፤ በቅርሱ ፤ በታሪኩና በስነ-ም ግባሩ እንደመሆኑ መጠን አገራችን ኢ ትዮጵያና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ ተ ክርስቲያናችን ባሕልን ፤ ቅርስንና ኪነ-ጥበብን ከሁሉም በላይ ነፃነትን ከ ትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፉ መቆየታቸው አይዘነጋም ። አሁን ያለ ውም ትውልድ ለነገው ትውልድ ቅርሳ ቅር ስን ጠብቆ የማስተላለፍ የታሪክ ግዴ ታ አለበት ።

ለምሳሌ ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ከተማ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ያሠሩአቸ ው አብያተ ክርስቲያናት ምንም እንኳ ን በረዥም ጊዜ ታሪካቸውና በሥነ-ጥ በብ ቅንብራቸው በሌላው ክፍለ ኢት ዮጵያ እጅግ የሚያስደንቁ ባይታጡም በመሠረቱ ሥዕሎችና ሐረጐች በጣም የሚያምሩ ከመሆናቸውም ሌላ የሕን ፃዎቹም አሠራር በጣም ጠንካራ ነው። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ አንድ አንድ አብ ያተ ክርስቲያናት የውስጥ ሥዕላቸውና የውጭ አካላቸው በመታደስ ላይ ስለ ሚገኙ ጥንታዊ ይዘታቸውን እንዳያጡ በእድሳቱ ሂደት ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል ።

ከዚህ ላይ አንባብያን እንዲረዱት የሚፈለገው የሚያፈሱ አብያተ ክርስ ቲያናት አይከደኑ ፤ ያረጀ ቤተ ክርስቲ ያን አይታደስ ማለት አይደለም። ፍሳሽ ንና ልዩ ልዩ ምክንያቶችን ካልተከላከ ልን ቅርሳችን ይወድማል።ይህም የቀደ ሙት አባቶቻችን ጠብቀውና ተንከባክ በው ያቆዩልን የባሕል ቅርስ የአሁኑ ትውልድ በመካከለኛው ዘመን ከተሠ ሩት ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ሥዕልና ሐረግ ፤ ከተጻፉት መጻሕፍት ጋር የጊዜውን ምርምርና ጥበብ ማወዳ ደር እንዲቻል በእድሳቱ ሥራ ጥንቃቄ ይደረግበት ፤ የሚታደሱት አብያተ ክ ርስቲያናትና ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ ጥን ታዊ ቅርስነታቸውን እንዳያጡ በአዋ ቂዎች እየተጠና ይታደሱ ማለት ነው ።

ከፍያለው መራሒ



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግዕዝ

# የግዕዝ ትምህርት

## ትምህርት ፳

### ረባሕ አንቀጽ

በግእዝ ቋንቋ አንድን አንቀጽ በዐሥር መራህያን ለማርባት ስንፈልግ በተወሰ ኑ ፊደላት እንጠቀማለን ። ለምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ኩ | ነ |
| ከ | ክሙ |
| ግእዝ ፊደል | ካዕብ ፊደል |
| ግእዝ ፊደልና ት | ራብዕ ” |

እነዚህም ፊደላት አንቀጻውያን ተውላጠ ስም ይባላሉ ።

መክሥት፡- ከዚህ በላይ ባጠናናቸው ፊ ደላት አንድን አንቀጽ እንዴት አድርገ ን በማርባት እንደምንጠቀም ቀጥሎ እ ንማራለን ። በመጀመሪያ አንቀጹን በአ ርእስት መደብ እንጽፋለን ።

| | | |
|---|---|---|
| ነቢር | ነቢሮት | መቀመጥ |
| ነጊር | ነጊሮት | መንገር |
| ከፊል | ከፊሎት | መክፈል |
| ሰኪብ | ሰኪቦት | መተኛት |
| ወሲድ | ወሲዶት | መውሰድ |
| ፈቲድ | ፈቲዶት | መፍቀድ |
| ቀፂብ | ቀፂቦት | መጥቀስ |

አሁን “ ነቢር ” የሚለውን አንቀጽ እ ንውሰድና ለማርባት እንሞክር ።

| | |
|---|---|
| ነበርኩ | ተቀመጥሁ |
| ነበርከ | ተቀመጥህ |
| ነበርኪ | ተቀመጥሽ |
| ነበረ | ተቀመጠ |
| ነበረት | ተቀመጠች |
| ነበርነ | ተቀመጥን |
| ነበርክሙ /ተባ/ | ተቀመጣችሁ |
| ነበርክን /አን/ | ተቀመጣችሁ |
| ነበሩ /ተባ/ | ተቀመጡ |
| ነባራ /አን/ | ተቀመጡ |

ከዚህ በላይ ባጠናነው ረባሕ አንቀጽ ዐረፍተ ነገር ለመሥራት እንድንችል የሚከተሉትን ቃላት እንመልከት ።

| | |
|---|---|
| ዲበ | በ-ላይ |
| ላዕላ | በ- ላይ |
| መንበር | ወንበር |
| ዐራት | አልጋ |
| ፀፍጸፍ | ደረጃ |
| ሕዋር | ወለል |
| ባሕቱ | ነገር ግን |
| መንጸፍ | ምንጣፍ |
| ዘእንበለ | ያለ |
| እንበለ | ያለ |
| አዕሩግ | ሽማግሎች |

## ዐረፍተ ነገር

አነ ነበርኩ ላዕለ መንበር
አንተ ነበርከ ዲበ መንበርከ
አንቲ ነበርኪ ዲበ መንበርኪ
ባሕቱ ውእቱ ነበረ ላዕለ ዐራት
ነበረት አስቴር ላዕለ ፀፍፀፍ
ንሕነ ነበርነ እንበለ መንፀፍ
ባሕቱ አንትሙ ነበርክሙ ዲበ መንፀፍ
ተባ

እኔ በወንበር ተቀመጥሁ
አንተ በወንበርህ ላይ ተቀመጥህ
አንቺ በወንበርሽ ላይ ተቀመጥሽ
ነገር ግን እርሱ በአልጋ ላይ ተቀመጠ
አስቴር ደረጃ ላይ ተቀመጠች
እኛ ያለምንጣፍ ተቀመጥን

ነገር ግን እናንተ በምንጣፍ ተቀመጣ ችሁ

አንተን ነበርክን ላዕለ አራት ክን
አዕሩግ ነበሩ ዲበ ፀፍፀፍ (ተባ)
አዋልድ ነበራ ላዕለ ምድር ዘእንበለ መንፀፍ
(አን)

እናንተ በአልጋችሁ ላይ ተቀመጣችሁ
ሽማግሎች በደረጃ ላይ ተቀመጡ
ሴቶች ልጆች በምድር ያለምንጣፍ ተቀመጡ ።

# መምህር ሣህሉ ተ/ማርያም



መምህር ሣህሉ ተክለ ማርያም ከአባታቸው ከመምሬ ተክለ ማርያምና ከእናታቸው ከወይዘሮ ደስታ ምክረ ሥላሴ በሸዋ ክፍለ ሀገር ሩፋ ማርያም ተወልደው ዕድሚያቸው ትምህርት ለመቀበል ሲደርስ የግዕዝ ንባብና አማርኛ እንዲሁም ጸዋትወ ዜማ አጠናቀው ከአወቁ በኋላ ቆፍና አማኑኤል ከታወቁት የቅኔ ባለቤት ከሆኑት ከአለቃ ምሥራቅ ዘንድ የቅኔ ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቀው ተመርቀዋል ።

ዕውቀታቸውን ከፍ በማድረግና ሀገራቸውንና ወገናቸውን ለመርዳት አስበው በፈረንሣይ ት ቤት ገብተው ተፈላጊውን ዘመናዊ ዕውቀት ገብይተዋል።

ከ1926 ዓ.ም ህዳር 7 ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 23 ቀን 1928 ዓ.ም. ድረስ በቀይ መስቀል ማኅበር ውስጥ አገልግለዋል ።

ከግንቦት 1 ቀን 1935 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 30 ቀን 1943 ዓ.ም. የትምህርት ሚኒስቴር ባልደረባ ሆነው በመምህርነት አገልግለዋል ።

1945ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1967 ዓ.ም. ጥር ወር ድረስ በሲዳሞ ክፍለ ሀገር የገንዘብ ሚኒስትር ተጠሪ ጽ ቤት ባልደረባ ሆነው በልዩ ልዩ የሥራ መስክና በገንዘብ ያዥነት ሲአገለግሉ ቆይተው የጡረታ መብታቸውን አግኝተዋል ።

በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከአገኙት መልካም ዕድል አንደኛው ወ/ሮ ሙሉነሽ አፈወርቅ ከሚባሉት የሕግ ባለቤታቸው 5 ሴትና 6 ወንዶች ወልደው በሥነ ሥርዓት አሣድገው በከፊል ሥራና በትዳር ላይ የሚገኙ ሲሆን የከፍተኛ ትምህርት ደረጃቸውን የሚከታተሉም አሉ ።

በጡረታ ክልል ከተመደቡ ወዲህም ሆነ በሥራ ዓለም ላይ ሣሉ የተቀበሉትን የሥልጣን ክህነት አደራ ሳያ ጠፉ ቀን ከሌሊት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚደረገውን አገልግሎት ደከመኝ ልረፍ በማይሉበት ሁኔታ ሲአገለግሉ ከመቆየታቸውም ሌላ ከህናቱም ሆኑምእመናኑ ለዕውነት የቆሙ አባት መሆናቸውን ስለሚያምኑባቸው በአሉበት ከተማ ይርጋ ዓለም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በአንደኛና በሁለተኛ ዙር እየተመረጡ በሰበካ ጉባኤ አባልነት ጭምር ሲአገለግሉ ቆይተው ምን ጊዜም ቢሆን ለሰው ልጅ ሞት የሚባለውዕዋዕከፈጣሪው የታደለው ዕዳ እንደመሆኑ መጠን በአደረባቸው ድንገተኛ ሕመም ምክንያት ሰኔ 25 ቀን 1973ዓ.ም. በተወለዱ በ64 ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው በይርጋ ዓለም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በ26፡10 73 የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው ተፈጽሟል።

በቀብራቸው ዕለት የሶስቱ አድባራት የወጣት መንፈሳዊ ማህበራት አባላት እንባ በእንባ እየተራጩ በከባድ ሀዘን ሲሸኙአቸውናእንዲሁም ካህናትበዝማሬ ምዕመናን በሃዘን የሚያካሂዱት የአስከሬን አሸኛኘት ለቁም ተመልካች ሞት ዛሬ ይምጣ የሚያሰኝ ክርስቲያኖችን ሁሉ የሚያስቀና አሟሟት ነበር ነገር ግን መምሬ ሣህሉ ተክለ ማርያም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ማዘን የሚገባቸው ቤተ ሰቦቻቸው ብቻ ሣይሆኑ ለባህሏና ለሥርዓቷ አስከባሪ ለምእመናን አርበኞች አጠናካሪ የሆኑ አባትና መምህር ስለተቀነሰባት ቤተ ክርስቲያንንም ከፍተኛ ሃዘን ተሰምቷታል ።



# የሥጋ ደዌ በሽታ

የሥጋ ደዌ በሽታ በብዙ ሀገሮች ይገኛል ። በሀገራችንም በተለይ በሸዋ ፣ በወሎ፣በጐጃም በጎንደርና በሐረርጌ ጐልቶ ይታያል ። ስለበሽታው አመጣጥ ሰዎች የተለያየ አስተሳሰብ አላቸው ነገር ግን የበሽታው አመጣጥ እነርሱ እንደሚሉት በሽታው ከያዘው ሰው ጋር በአንድ የውኃ ጉድጓድ ወይም ምንጭ በመጠቀም በዘር ...... ወ.ዘ.ተ. የሚተላለፍ ሳይሆን በባክቴሪያ (በጀርም) ነው ።

ብዙ ዓይነት ተላላፊ በሽታዎች እንደመኖራቸው መጠን የሥጋ ደዌ በሽታም ከእነርሱ ውስጥ አንዱ ነው ። ከሰው ወደ ሰው ለመተላለፍ ግን ረዥም ጊዜና የረዥም ጊዜ ንክኪ ስለሚጠይቅ እንደሌሎቹ አስጊ አይደለም ።

የሥጋ ደዌ በሽታ ከሰውነት ላይ የሚወጣው በተለያየ መልክ ቢሆንም ዓይነቱ ግን ሁለት ነው ። ከሁለቱም ውስጥ ተላላፊው 1ኛው ብቻ ነው ። በመመሪያ ጊዜ በሽታውን መደበቅ ስለሚቻል በሽተኞች ይህንን ለማድረግ ይሞክራሉ በዚህ ጊዜ ለቤተሰቦቻቸውና ለጓደኞቻቸው ይተላለፋል ። ይሁን እንጂ ሰዎቹ በሽታውን የመቋቋሚያ ኃይል ካላቸው ላይተላለፍባቸው ወይም ላያጠቃቸው ይችላል ።

የሥጋ ደዌ በሽታ ብዙ የኋላ ጣጣ የሚያስከትል በመሆኑ በሽታውን ለማጥፋት ጊዜ መስጠት አያስፈልግም ። ሌሎችንም መበከል የተገባ አይደለም። በእርግጥ ሰዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ስለበሽታው አመጣጥየተለያየአመለካከት ስላላቸው በተጨማሪም ሊያድን የሚችል መድኃኒት የለም ብለው ስለሚያስቡ ወደ ጤና ባለሙያዎች ከመምጣት ይዘገያሉ ጭራሽ የማይመጡም አሉ ። በሽታው ከሰው ወደ ሰው የሚጋባው ወይም ሰውየውን የሚያጠቃው ከረዥም ጊዜ በኋላ እንደመሆኑ የሚድነውም በረዥም ጊዜ ሕክምና ነው ። ይሁን እንጂ በቆዳ ላይ የተለያዩ ምልክቶች እንደታዩ ማለትም በሽታው እንደጀመረ ወዲያውኑ ወደ ሕክምና ባለሙያዎች ከሄዱና ሌላ ዓይነት የቆዳ በሽታዎች ስላሉ የሥጋ ደዌ በሽታ መሆኑ ከተረጋገጠ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመዳን ይቻላል ። እንዲሁም ከታከሙ ወይም መታከም ከጀመሩ በሽታው ወደሌሎች አይተላለፍም ።

የሥጋ ደዌን በሽታ ሊያመጡ የሚችሉ ጀርሞች የሚያጠቁት የስሜት ሕዋሳትን (ነርቮችን)ና ቆዳን ሲሆን የሚታየው በተለይ በፊት፡በእጅና በእግር ላይ ነው ። በሽታው ሲጀምር የተለያዩ ምልክቶች በቆዳ ላይ ይወጣሉ ፣ የፊትና የጆሮ ቆዳ መወፈር የማቃጠል ስሜት ፣ የእጅና የእግር ጣቶች ስሜት ማጣት ወይም መደንዘዝ እንዲሁም ኃይል ማነስ ይኖራል ። በዚህ ደረጃ ካልታከመ ሌላ ምልክቶችን ማሳየት ይጀምራል ። የቅንድብ ፀጉር ይመለጣል የአፍንጫ ቅርጽ የተለየ ይሆናል የእጅና የእግር ጣቶች ይጐብጣሉ ወደ ውስጥ ይቆለፋሉ ። በነርቮቹ መሞት ምክንያት የእጅ የእግር ፣ የፊት ሽባነትና መጣመም ሊኖር ይችላል ። እንደዚሁም ጀርሞቹ በዓይን ላይ በመቀመጥ የዓይን ቅላት ፣ ማቃጠል፡ እንባ ማፍሰስ ፣ የማየት ኃይል መድከም በተለይም በፀሐይ ብርሃን ማየት አለመቻልን ያስከትላል ። በእንቅልፍ ጊዜም የአይናቸው ቆብ ስለማይከደን በዓይን ላይ ብዙ ጉዳት ይደርሳል። ስለዚህ ለዓይናቸውም ካልተጠነቀቁና ካልታከሙ የመታወር ዕድል ያጋጥማቸዋል ።

የሥጋ ደዌ በሽታ ጀርሞች ቁምጥናን ወይም አካለ ስንኩልነትን እያመጡም ይሁን እንጂ ይህ በሽታ የያዛቸው ሰዎች ከፍርሃትም ሆነ ከሃፍረት የተነሳ በሽታውን ለመደበቅ ስለሚሞክሩ በሌላ አንጻርም ብዙዎች የበሽታውን ምንነት በቶሎ ስለማይረዱት በሽታው ከተባባሰ ደረጃ እስከሚደርስዝም ይላሉ ። ከዚያም ቀደም ሲል እንዳየነው የስሜት ሕዋሳት ይሞታሉ በዚህ ጊዜ እሳት ቢያቃጥላቸው ስለት ቢቆርጣቸው ምስማርም ይሁን የጠርሙስ ስባሪ እግራቸው ውስጥ ገብቶ ቢቀር ሊያውቁት አይችሉም ሕመሙ አይሰማቸውምና ። በእነዚህ የተለያዩ ጉዳዮች ሳቢያ ቁስል ይመጣል ። ሕመሙም ባለመሰማቱ ምክንያት የተጐዳውን የአካል ክፍል ስለማያሳርፉት የመዳኑ ሁኔታ የመነመነ ይሆናል ፣ በተጨማሪም በሽተኞቹ ራሳቸውን ከሰው በታች አድርገው ስለሚገምቱ ስለሰውነታቸው ስለልብሳቸውና ስለአካባቢያቸው ንጽህና ደንታ ቢሶች ይሆናሉ ። የንጽህና ጉድለትም ለቁስሉ መበከል ዋና ምክንያት ይሆነዋል ሌላው የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ አንዳንድ በሽተኞች ከአሁን በኋላ ሥርተን መብላት አንችልም ብለው በማስብ ለልመና እንዲያመች በማለት እያወቁም ቢሆን ሰውነታቸውን ለጉዳት የሚያጋልጡ መኖራቸው ነው ። በዚህ ዓይነት የአካል መጉደል ወይም ቁምጥና ይመጣል ። ከዚህ በኋላ ማለት ሕመሙ አስከፊ ከሆነ ደረጃ ከደረሰ በኋላ ቢታከሙ የሚረዳው ጀርሞቹን በማጥፋት ሊከተል የነበረውን ችግር ማስቀረት ብቻ ነው ። ቁስሉንም ማዳን ይቻላል ። ይሁን እንጂ የጠፋውንና የሞተውን የስሜት ሕዋስ ለመመለስ ወይም የተቆረጠውንና የጐደለውን የአካል ክፍል እንደነበረ የሚያደርግ መድኃኒት የለም ። ቢሆንም በቀዶ ጥገና የሰውየውን ችግር ለማቃለልና በተሻለ መንገድ ለመርዳት ይቻላል ።

የሥጋ ደዌ ያለባቸው ሰዎች በሽታ

ወደ ገጽ ፳፬ ዞሮአል



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## የሴቶች ምስክርነት

አንድ ሰው ያየውን የሰማውንና በራሱ ላይ የተደረገለትን ነገር በእውነት ያለ ሐሰት ለሌላው በገንዘብ ተገዝቶ ሳይሆን ስለ እውነት በእውነት ሲናገር እውነተኛ ምስክር ይባላል ቃሉም የታመነ ይሆናል፡

ክርስቶስ ለሰው ልጆች ደኅንነት ሲል ወደዚህ ዓለም መጥቶ ብዙ መከራና ስቃይ እንደተቀበለና አዳኝ አምላክ እንደሆነ ብዙ ሰዎች መስክረዋል የክርስቶስን አዳኝነት የመሰከሩና በአምላክነቱ ያመኑ ወንዶች ብቻ እንዳይደሉ መጻሕፍት ይናገራሉ ። ሴቶችም በሰዎች ፊት ስለክርስቶስ መስክረዋል ለምሳሌ ያህል ጵርስቅላ የተባለችው ሴት የእግዚአብሔርን ቃል በእውነት የተረዳች ስለነበረች ቃሉን ለሌሎች መስክራለች የክርስቶስን አዳኝነት ገልጣ አስተምራለች ።

' ጵርስቅላ ከባልዋ ከአቂላ ጋር ድንኳን እየሰፋች የምትኖር ሴት ነበረች ጵርስቅላና አቂላ በፊት በቆሮንቶስ ከተማ ይኖሩ ነበሩ በኋላ ግን ከጳውሎስ ጋር ወደ ኤፌሶን ሄደው በዚያ ቤት ሠርተው መኖር ጀመሩ በኤፌሶን ሳሉ ጵርስቅላ ከባልዋ ጋር በመሆን አጵሎስ የተባለውን ምሁረ ኦሪት በመምከር ከበፊቱ ይልቅ የእግዚአብሔርን መንገድ ገለጠችለት ጵርስቅላ እጅግ ደግ እንግዶችን ተቀባይና አስተናጋጅ ከመሆንዋ የተነሣ ቤትዋ የክርስቲያኖች ሁሉ መሰብሰቢያ ሆኖ ነበር

ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ደብዳቤ ሲጽፍ " በጵርስቅላ ቤት ያለች ቤተ ክርስቲያንን ሰላም በሉልኝ" እያለ ይጽፍ ነበር የሐዋ ሥራ 18፡2-3 ፡ 18 24- 28 ሮሜ 16፡3-5 1ኛ ቆር 16 ፡ 19 ፡ 2 ጢሞ 4 ፡ 19

በሰለጠኑት አገር የሚገኙት ክርስቲያን ሴቶች ስለ ክርስቶስ ለመመስከር ብዙ ዕድል አላቸው ይህም የቤት እመቤቶች እንደመሆናቸው መጠን በቤታቸው ሰዎችን በማስተናገድ ጊዜ ቃሉን ሊያስተላልፉ ይችላሉ ።

ወደቤታቸውም ሰዎች እንዲገቡና እንዲያስተናግዱ የመፍቀድ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ያላቸው በብዙ ሀገሮች ሴቶች ናቸው ። ስለዚህ እውነተኞች ክርስቲያን ሴቶች የመምከርና የማስተማር የመመስከርም ዕድል ይኖራቸዋል በተለይም የንግግር ለዛና ተወዳጅነት ኣላቸው ቢናገሩ ይደመጣሉ ቢመሰክሩ ይታመናሉ ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ክርስቶስ የመሰከሩ ቃሉን የተናገሩ አዳኝነቱንም ያወሩ ብዙ ሴቶች አሉ ።

በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 4 ውስጥ የተጠቀሰችው ሳምራዊት ሴት ክርስቶስ ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት በተስፋ ይጠበቅ የነበረው መሲሕ እንደሆነ ለሰማርያ ሰዎች ሁሉ መስክራለች ይህች ሴት ውሃ በምትቀዳበት ጊዜ ጌታችን ኢየሱስን አገኘችው እርሱ ራሱ የሕይወት ውሃ እንደሆነ ነገራት ።

እርሷም የነገራትን ሁሉ ለሰማርያ ሰዎች ለመንገር እንሰራዋን ትታ ሄደች ። የሰማርያ ሰዎች በሴትዮዋ ምስክርነት የሰሙትን በዓይናቸው ለማየት በነቂስ መጡ አይተውም አመኑ በሀገራቸውም እንዲቀመጥ ለመኑት ።

ሴትዮዋ ከዚህ በፊት አስተማሪ አልነበረችም በጠባይዋም የምትመሰገን አልነበረችም ። ግን ጌታችን ኢየሱስን ባገኘችው ጊዜ ጠባይዋ ሁሉ ተለወጠ ስለእርሱም ለመመስከር በቃች ።

በዚህች ባልተጠበቀችው ሴት ምስክርነት የሰማርያ ሰዎች አምነው ዳኑ ። በዚህ አንጻር እያንዳንድዋ ሴት በተሠማራችበት የሥራ መስክ ሁሉ ልትመሰክር ትችላለች ውሃ የሚቀዱ በሚቀዱበት ጊዜ ጸሐፊዎች በቢሮአቸው የቤት እመቤቶች በቡና ሰዓታቸው በጠቅላላ በማንኛውም የሥራ መስክ ያሉ ሴቶች ስለ ክርስቶስ መነጋገርና መመስከር እንደሚገባቸው ከጵርስቅላና ከዚህች ሳምራዊት ሴት መማር ይችላል ።

ከዚህም ሌላ ከላይ የተጠቀሱት እነዚህ ሴቶች እምነታችንንከሥራ ላይ እንድናውለው ያስተምሩናል ። እውነተኞች ክርስቲያኖች ሁሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት የወንጌል መልእክተኞች ናቸው እግዚአብሔርን በሚገባ ራሳቸው ካወቁ ከሌሎች ጋር ሊያስተዋውቁ ይፈልጋሉ ። የሚያድናቸውና የሚቀድሳቸው እውነት ልባቸውን ፈንቅሎ ይወጣል ። ከሕያው ምንጭ የጠጡ ሁሉ ራሳቸው የሕይወት ፏፏቴ ይሆናሉና በሕይወት ውኃ ጥማት ሊሞቱ የተቃረቡትን ስለሚፈውስ ዙሪያውን እንደምታለመልምና እንደምታረካ የበረሃ ምንጭ ነው ።

ስለዚህ ለራሳችን ጥቅም ብቻ ከምንፍጨረጨር ይልቅ ሌሎችን የምናውቀውን እውነት በማስተማር ለመርዳት ብንሞክር የበለጠ በረከትና ዋጋ እንቀበልበታለን ። ታማኝ ሴት ለባልዋ ርግጠኛ ምስክር ናት ፡ መልካም እናት ለልጆችዋ የማትጠረጠር ምስክር ናት ስለሆነም ሴቶች የክርስቶስን አምላክነት ፡ ቸርነቱንና አዳኝነቱን ለመመስከር በማንኛውም ጊዜና ቦታ ይችላሉ ።



# ቤተ ክርስቲያን ለሕብረተሰቡ የምታስተላልፈው መልእክት

ቤተ ክርስቲያን በመምህራን ፡ በሊቃውን ፡በአባቶች መልእክትዋን ለክርስቲያናዊ ሕብረተሰብ ስታስተላልፍ ኖራለች መልእክትዋንም የሚቀበልእን ዴት ያለ ሕብረተሰብ ነው ? እምነትን ምግባርን ጠንቅቆ ያወቀ የተረዳ የኑሮ ትግልና የመንፈስን እድገት ፡ ሥነ ሥርዓት ሕግጋት በትክክል ያወቀ ነው ።

እንዲህ ያለውም ህብረተሰብ ለሁሉ ነገር የተዘጋጀና ቤተ ክርስቲያንም ያስተላለፈችውን መልእክት ተቀባይ ስለሚሆን በክርስቶስ መንፈስ የበረታ ይሆናል ። ከዚህ የተነሳ ቤተ ክርስቲያን የምታስተላልፈውን መልእክት መስማት ብቻ ሳይሆን በተግባር ላይ ያውላል።

ይህ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን በአባቶች በመምህራን ያስተላለፈችው መልእክት ምን ነበር የሚል ጥያቄ ቢቀርብ በቅደም ተከተል እናቀርባለን መጥምቁ ዮሐንስ የሚገባ የንስሐ ፍሬ አድርጉ እያለ በሚያስተምርበት ጊዜ ፡ ሕዝቡ ምን እናድርግ እያሉ ጠየቁት መልሰም «ሁለት ልብስ ያለው አንዱን ለሌለው ያካፍል ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ አለ ። ሊጠመቁ የመጡት ቀራጮች ደግሞ መምህር ሆይ እኛም በበኩላችን ምን እናድርግ ሲሉ ጠየቁት ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ አላቸው። ሰላም አስከባሪ የነበሩትም ጭፍሮች እኛ ደግሞ በበኩላችን ምን እናድርግ ሲሉ ጠየቁት እርሱም በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ ፡ ደመወዛችሁም ይብቃችሁ » አላቸው የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፫ ከቁጥር ፲ - ፲፬ ።

ይህ መልእክት የተላለፈው ያን ጊዜ ለነበረው ሕብረተሰብ ብቻ ሳይሆን አሁንም ላለው ህብረተሰብ ጭምር መሆኑን ልንረዳ እንችላለን አባባሉን የተመለከትን እንደሆነ ረሃብ ፡ መታረዝ በሽታ ወገን ዘርን ሃይማኖትም እንደማይለይ ሁሉ ስጦታም ፡ አገልግሎትም ፡ እርዳታም ለሁሉም በእኩልነት ሊሰጡ ያስፈልጋል ። እኛ በድሎት በምቾት እየኖርን ሌሎች በችግር ቢያልቁ እኛ በየቀኑ ልዩ ልዩ ልብስ እየመረጥን እየለበስን ፡ ሌሎች እራቁታቸውን ሲሄዱ ከተመለከትን ፡ ሠልጥነናል ፡ ክርስቲያኖች ነን ብንል ሐሰተኞች ነን ።

በተጨማሪም ዮሐንስ በሚያስተምርበት ወቅት ለጠየቁ ሰላም አስከባሪዎች ደመወዛችሁ ይብቃችሁ ያለው እነሱን ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ሠራተኛ ደመወዙ ብቻ እንዲበቃው ፡ በገዛ ላቡ እንዲጠቀም እንጂ በሌላው ላብ እንዳይከብር በሚገባ ሠርቶ የሚገባ ፍሬ እንዲያፈራ ነው ። ይህም መልእክት የሚያስተምረን ሁሉም ተደጋግፎ መኖር እንደሚገባውና አንዱም ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌላው ጭምር የሚኖር መሆኑን ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በህብረተሰቡ መካከል ተገኝቶ ሳለ የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት "መጽሐፉን በገለጠ ጊዜ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል ለታሠሩትም መፈታትን ፡ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ ልኮኛል" ብሏል ። የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ከቁጥር 17 - 21 ።

ይህ ቃል የሚያስተምረን ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለተራበው ሕዝብ የሕይወት እንጀራ ሊሆንና ድሆች የህይወት እንጀራ የሚያገኙባትን አቅጣጫ ቤተ ክርስቲያንለህብረተሰቡ እንድታሳይ መታዘዙዋንና መልእክትም እንድታስተላልፍ ነው ። ወንጌልም ለድሆች ተሰበከ ሲባል መጀመሪያ እኩልነትን ራስን መግዛትን ቀጥሎ ራስን በራስ መምራትን ከዚያም በሌላ ወዝ መክበር ሣይሆን በራስ ወዝ ሰርቶ መክበር ራስን ማክበር ነው ። ይህም ለምንሰራው ሁሉ ታላቅ የምሥራች ነውና ።

የወንጌልም ትምህርት የሚለው እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ አባት ነው ። ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ወንድማማቾች ናቸው ። በእርሱም ፊት አንዱ ከአንዱ አይበልጥም ይላል ። ለድሆች ወንጌልን መስበክ ማለትም ቃሉን ብቻ ማስተማር አይበቃም ጥሩ ምሳሌ እየሆኑ ቃሉን በሥራ ገልጦ ማሳየት ያሻል ድሆችን ለመርዳት ድሆችን ለማገልገል ፡ መጀመሪያ ድሆችን መውደድ ያስፈልጋል ምንም እንኳ ሰዎች በተፈጥሮ እኩል ቢሆኑም በልዩ ጠባያቸው ይለያያሉ ። እነዚህንም ልዩነቶች ማስወገድ እንጂ ማክበር አይገባም ። ምክንያቱም ሰዎች በዚህ ዓለም በኑሮ ቢለያዩም በሞት ስለማይለያዩ እኩልነት አላቸው ማለት ነው ።

ለምሳሌ የሰውን ሕይወት ወይም ኑሮ በዓሣ ልንመስለው እንችላለን ዓሣ በባሕር ውስጥ እስካለና በመረብ እስኪያዝ ድረስ ነፃ እንደሆነ ሰውም ተወልዶ እስከ ሞተ ድረስ ነፃ ሊሆን ይገባል።ነፃነትም ማለት ወገንዘመድ ሳይለይ ከድሆች ጋር የኖረ እንደሆነ ነው ከመቀበል መስጠት ይሻላል ይላልና ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የምታስተላልፈው የወንጌል መልእክት እኩልነት ፡ ማህበራዊ ኑሮን ለህብረተሰቡ የሚያስከብር ታላቅ የምስራች ነው ሊባል የሚገባው በዚህ አኳኋን የተመራ እንደሆነ ነው ።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ህብረተሰቡ እርስ በርሱ መረዳዳትና መተሳሰብ እንደሚገባው ቅዱስ ጳውሎስ ያስተላለፈው መልእክት እንዲህ ይላል " እርስ በርሳችሁ በአንድ አሣብ ተስማሙ ፡ የትዕቢትን ነገርአታስቡ ።ነገርግንየትህትናን ነገር ለመሥራት ትጉ ። ልባሞች የሆናችሁ አይምሰላችሁ ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ በሰው



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ሮሜ ምዕራፍ ፲፪ ፥ ከቁጥር ፲፯ - ፲፰ ።

መልእክቱ እንዳለው ማንኛውም ሀብረተሰብ ከሰዎች ጋር በሰላም መኖር ያስፈልገዋል በሰላም መኖርም ማለት አብሮ መብላት ፤ አብሮ መጠጣት ፤ አብሮ መሥራት፤አካባቢን፤ጐረቤትን መስሎ መኖር ነው ይህ ከተፈጸመ በህብረተሰቡ መካከል ሰላም አለ ይህም ሲባል ሌላው እየተራበ እኛ ብንጠግብ ጐረቤቶቻችን እያዘኑ ፤ እያለቀሱ እኛ ብንደሰት ፤ በአካባቢያችን ያሉት ወንድሞቻችን እራቁታቸውን እየሄዱ እኛ እያማረጥን የምን ለብስ ከሆነ መለያየት እንጂ ሰላም የለም ። ከዚህም የተነሳ ቤተ ክርስቲያን ያስተላለፈችውን መልእክት መስማት እንጂ መሥራት አንችልም ማለት ነው ። እንዲህ ያለው ሁኔታ የተግባር ድሐ ስለሚያደርገን የቤተ ክርስቲያንን መልእክት እንዳናከበርን ያስቆጥረናል ።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ባለንበት ዘመን አንድ የምስራቅ ቤተ ክርስቲያን መሪ ስለ መሳሪያ ቅነሳ ለህብረተሰቡ ያስተላለፈው መልእክት እንዲህ ይላል ። "የጦርነት ወሬዎች በየቀኑ ከየአቅጣጫው ይደርሱናል ሰምተንም ከጉዳት በቀር ጥቅማቸውን ልንረዳ አልቻልንም ዓለም ሰላምን ትሻለች ሰላም ግን የለም ለእድገት ለትምህርት ለጤንነት ከሚወጣው ገንዘብ ይልቅ ለጦር መሣሪያ የሚውለው ገንዘብ እጥፍ በመሆኑ ሰላም ቀዝቅዟል ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በመጀመሪያ በጐናችን ያለውን መርዳት ነው እንደዚህ ብናደርግ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወዳጆች ይኖሩናል ። እንዴት ለሁሉ ማድረግ እንችላለን በማለት ኑረን ኑረን አንድ ቀን አንድ ነገር ለአንድ ሰው እናደርግ ይሆናል ነገር ግን በዚህ መንገድ የድሆችን ችግር አቃለልን ለማለት አንችልም አንዱ አንዱን የማይረዳ ከሆነ ሕብረተሰብ ተፈላጊ አይደለም ማለት ነው ሰዎች ሰላምን ሊያገኙ አይችሉም ። በዚህ መካከል መቆሚያው የት ነው ?

ቅዱስ ጳውሎስ በአንደኛ ቆሮንቶስ በምዕራፍ ፲ በቁጥር ፲፪ እንዳለው "ስለ ዚህ እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ ።" ብሏል ።

ሌላው ደግሞ "በአሁኑ ጊዜ አሜሪካ እሠራለሁ እያለች ዓለምን የምታስፈራራበትን ኒውትሮን የተሰኘው ሌላው አደገኛ ቦምብ እንዳይሰራ ሰላም ወዳድ ድርጅቶችና ግለሰቦች በተቃውሞ ላይ ይገኛሉ ።

በዚሁ መሠረት የኖርዌይ ሊቀ ጳጳስ ይኸው ኒትሮን ቦምብ ተሠርቶ በሙከራ ላይ እንዳይውል ያለውን ተጽዕኖ ሁሉ እንዲያደርግ መንግስታቸውን ጠይቀዋል ።"

በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን አዘጋጅነት በታንዛንያ በአሩሻ ላይ ጥቅምት ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. የተሰበሰበው የምክክር ጉባኤ በደቡብ አፍሪካ ያለውን የዘር መድልዎ ጨቋኝ ሥርዓት ለመለወጥ ጥረት እንዲያደርጉ ለድርጅቶችና ለመንግሥታት ጥሪ አቀረበ ። በተጨማሪም የኢኮኖሚ የባህልና የጦር መሣሪያ ዕገዳ እንዲያደረግ ጠይቋል "

ብፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስም መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. በመስቀል በዓል አከባበር ላይ ለህብረተሰቡ ባስተላለፉት የቤተ ክርስቲያን መልእክት "የዓለምን አመለካከት በሁለት መንገድ እናየዋለን ። 1ኛው ዘወትር የእግዚአብሔርን ቃል በግዞት ለማስቀመጥ ሲሆን ፪ኛው የእግዚአብሔርን ቃል በግልጥ መናገር ነው ።

ቢሆንም የእግዚአብሔር ቃል በቆሻሻ ውስጥ ተቀብሮ አይቀርምናንግሥት ዕሌኒ ከሐዋርያት በተማረችው ቃል እየተመራች መስቀሉን ለዓለም እንዲያበራ ልታወጣው ችላለች ። ለአይሁድ ስለ እግዚአብሔር ቃል ስንናገር የምን ሳሳት ይመስላቸዋል ። እንደተባለው ዛሬም ስለ መስቀሉ ስንናገር ለዓለም የምናብድ ይመስለው ይሆናል ። ይሁን እንጂ መስቀል ነፃ አውጭ መስቀልየእግዚአብሔር ኃይል ነው ካሉ በኋላ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ለዓለም የምታስተላልፈው መልእክት መስቀ ለኢይግፋዕ እስ መዘኢይትገፋዕ መስቀልንአይግፋ የማይገፋ ነውና" ብለው አስረድተዋል ።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ምድራዊት ብቻ ሳትሆን ሰማያዊትም እንደ መሆኑዋ መጠን ሰዎችም ምድራውያን ብቻ ሳይሆኑ ሰማያውያን ሆነውወደመስቀሉ እንዲሮጡ መልእክትዋን ማስተላለፍ ይገባታል እሩጫቸውንም ጨር ሰው ግቡን መቱ የሚባሉት ከመስቀሉ ጫፍ ሲደርሱ ነውና መልእክቷን ለህብረተሰቡ ሁልጊዜ ታስተላልፍ ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

---

## መልእክተ ገነት ጽጌ

ከገፅ ፱ የዞረ

መልስ ፡ ጉየተ ሕፃን አጉየየ ለዲያብሎስ (የሕፃኑ መሰደድ ዲያብሎስን መዳረሻ አሳጣው ፡ አሳደደው) ተብሎ ተጽፏል ስለዚህ በማኅሌቱ ላይ የሚታየው የደስታ ስሜት የሚመለከተው የክርስቶስን ሳይሆን የዲያብሎስን ስደትና ውድቀት ነው ።

ቤተክርስቲያንና ምእመናን በዲያብሎስ መባረር ለደስታቸው ወሰን የለውም" ።

ይኸንን ከዚህ በላይ የተገለጸውን ኃይለ ቃል የሰሙ ሁሉ ሊቁ ጊዜ ሳይወስድ ወዲያውኑ በሰጡት በዚህ አጥጋቢ መልስ አድንቀዋቸዋል ።

መልአከ ገነት ጽጌ ሻውል ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር ቃል ሲመሩ ከኖሩ በኋላ በተወለዱ በስድሳ አራት ዓመት ዕድሜያቸው በ1936 ዓ.ም አርፈዋል ።

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ



# የታመነ ካህን ለእኔ አስነሣለሁ

በዚህ ባለንበት ምድራዊ ዓለም ለሥጋዊ ሥራም ሆነ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ገንዘቡ ያልሆነውን የማይመኝ ያላስቀመጠውን የማያነሳ በያዘውም ሥራእምነት የሚጣልበት ሰው ሁልጊዜ ተፈላጊነት አለው ። ግን የያዘውን ሥራ ዘንግቶ በሚሠራው ሥራ ምን ጉድለት ይገኝብኝ ይሆን በማለት ራሱን በራሱ የማይቆጣጠርና ይሠራል ተብሎ ታምኖበት በኃላፊነት የተሰጠውን ሥራ ወደ ኋላ ትቶ ስለሥራው የማያስብ ከሆነ አለማሰቡና የማይታመን መሆኑን በሰው ዘንድ ስለሚታወቅ ተፈላጊነት አይኖረውም ምናልባት እንኳን እውቀት ኑሮት በእውቀቱ አማካይነት ከሥራ ገብቶ ሥራውን ቢጀምርም ጥቂት ጊዜ ሳይቆይ ጉድለት ሲገኝበት ወድያውኑ ባጎደለው ባጠፋው ጥፋት ከዚያው ከያዘው መልካም ሥራ በውድ ሳይሆን በግድ ተመንጥቆ እንደ ሚወጣ የተረጋገጠ ነው ። ይኸውም ደህና ተቆጣጣሪ ሲያገኝ ማለት ነው ።

አዎ ይህ በርእሱ ላይ የታመነ ካህን ለእኔ አስነሣለሁ የሚለው አምላካዊ ቃል ከዚህ ላይ ሊጠቀስ የቻለው ያለ ምክንያት አይደለም አንድ መነሻ አለው የቤተ እግዚአብሔር ዋና አስተዳዳሪ ዔሊ የሚባል ካህን ነበር ለዚሁም ካህን ሁለት ልጆች ነበሩት የልጆቹም ስም አፍኒንና ፊንሐስ ይባላሉ እንግዲህ እነዚህ ልጆች በመንፈሳዊ አስተዳደግ ካለማደጋቸው የተነሳ አምላካቸውን የማይፈሩ ለአባታቸውም የማይታዘዙ ከመሆናቸውም በላይ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ሰውንም የሚያስቀይም ከባድ የሆነውን ኃጢአት እየሠሩና በሕግ ወጥነት ኖሩ ።

አባታቸውም ዔሊ በአባትነቱ ሰው ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድበታል ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለ እርሱ የሚለምን ማን ነው? » በማለት ቢመክራቸውና ቢገሥጻቸው የአባታቸውን ቃል ሊሰሙ አልቻሉም ይኸውም ልጅ በሕፃንነቱ ካልተቀጣ ከጎለመሰ በኋላ ሊቀጣና ተቀጥቶም ልክ ሊገባ አይችልም ምክንያቱም «ልጅህን ካቀማጠልከው ይበረታታብሀዘንድወደ መበረታት ይመለሳል ከእሱ ጋርም ብትጫወት ጥርስህን ያረግፍሃል » ሲራ 30፡ 9 ተብሎ እንደ ተጻፈ እነዚህን ልጆች አባታቸው በመንፈሳዊ አስተዳደግ ሠርቶ ቀጥቶ አላሳደጋቸውም ነበርና ፤

ታዲያ በአመጸኞች ጠንቅ የሚመጣ ቁጣ ለፈቃደኞች ለደጋግ ሳይተርፍ ስለማይቀር እነሱ ባመጡት ስብብና እነ አፍኒን በፈጠሩት አበሳ ሁለቱ ማለትም አፍኒና ፊንሐስ በአንድ ቀን ሲሞቱ በቤትህም ሽማግሌ ለዘለዓለም አይገኝም የታመነ ካህንም ለእኔ አስነሣለሁ የሚል ቃል ከእግዚአብሔር ወደ ዔሊ መጣ 1ኛ ፡ ሳሙኤል 2 ፡ 35 በዚህም ምክንያት የእሳት ቃጠሎ በተነሣበት ወቅትእርጥቡንና ደረቁን ሳይለይ ሁሉን አብሮ እንደሚያቃጥለው ሁሉ አፍኒና ፊንሐስም ባመጡት ጠንቅየእግዚአብሔር ቁጣ በዔሊ ላይ ነደደ ዔሊም ከተቀመጠበት መንበር ወድቆ አንገቱ ተሰብሮ ሞተ 1ኛ ሳሙ4፡18 ከዚህ በኋላ ግን እግዚአብሔር የታመነ ካህን ለእኔ አስነሣለሁ ብሎ በተናገረው ቃሉ የታመነውን ካህን ሳሙኤልን ለእግዚአብሔር ነቢይ ይሆን ዘንድ የታመነ እንደሆነ አውቀ 1ኛ ሳሙ 3፡ 20 ሲል ያስረዳል ይህ ብቻ አይደለም በሌላም በኩል እግዚአብሔር እረኞች ባለመታመናቸው እጅግ ስላሳዘነው በነቢዩ በሕዝቅኤል ላይ አድሮ « በጎችን ከእጃችሁ እፈልጋለሁ በጎችንም ከማሰማራት አስተዋቸዋለሁ » ሕዝ 34 ፡ 10 የተናገረበትም ጊዜ አለ ይኸውም እግዚአብሔር በምድር ላይ የታመኑ እረኞችን ቢፈልግ ፈጽሞ ባለማግኘቱና በቀናው መንገድ እየመሩ በጎችን በትጋትና በንቃት ይጠብቃሉ ተብለውእምነት የሚጣልባቸው በማጣቱ ነበር ቢፈልግ ሁሉም ምንደኞች እንጂ እውነተኛ ሁነው ስላልተገኙ ነው ።

ይህ በጎችን ከእጃቸው እፈልጋለሁ የሚለው አስደንጋጭ ቃልና አስፈሪ አነጋገር በእግዚአብሔር ቃል ሊነገር የቻለውም ራሳቸውን እንጂ በጎችን የሚያሠማሩ እረኞች በብዛት ባለመኖራቸው ነው ።

እንግዲህ እረኞች ስንል ምን ማለታችንነው? በጎች ማለትስምን ማለትነው? አዎ ከሁሉ አስቀድሞ በእረኞች የተመለሉመንፈሳውያን መሪዎች ማለት ካህናት እንዲሁም በበጎች የተመሰሉት በክርስቶስ አምነው በታዘዘው ክርስቲያናዊ ተግባር ጸንተው የሚኖሩ ምእመናን መሆናቸውን ማወቅ ያስፈልጋል ።

አንድ ሰው ከተማረና የመምህራንን ደረጃ ከያዘ የመምህራን አገልግሎት ምን እንደሆነ መገንዘብና ማጥናት ይኖርበታል ሥራውንም ካጠና በኋላ መምህር እንደ መሆኑ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ቤተ እግዚአብሔርን ከማገልገሉም በላይ ምእመናኑንም ደግሞ በበለጠ ሁኔታ እየዞረ ማስተማር አምልኮተ እግዚአብሔርንም ማሳወቅ የተበተኑትን መሰብሰብ የተሳሳቱትንም መክሮና አስተምሮ ከስህተታቸው ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ የአንድ መንፈሳዊ መሪ ተቀዳሚ ተግባሩ መሆን አለበት የእውነተኛ መምህር ተግባር ይህ ነውና ። ግን መንፈሳዊ መምህር መሆኑን ተገንዝቦ ምእመናኑን እጠብቃለሁ በቀና መንገድም እመራለሁ ብሎ የመምህርነትን ደረጃ ከያዘ በኋላ ምእመናንን ማስተማሩንና መምከሩን ትቶ ምእመናኑ ሲበተኑ እያየ የማይሰበስብ መክሮና አስተምሮየማይመልስከሆነከዚህ ቀደም የነበረው ሐኬተኛው መምህር እንደ ተፈረደበት ሁሉ ዛሬም ቢሆን የማያስተምረውንና በመምህራን ዓይነት የማይመክረውን መምህር « አንተ ሐኬተኛ አገልጋይ » ተብሎ ከፍርድ እንደማያመልጥ ትክክለኛ ነው ።

መምህራን ሁነው የማያስተምሩና የማይመክሩ ከሆኑ የማስተማር ኃላፊነታቸውን በመዘንጋታቸውና የተጣለባቸውን እምነት አልጠበቁምና በእግዚአብሔርታላቅ ወቀሳ ብቻ አያመልጡም



www.ethiopianorthodox.org

ራሱ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማይታመኑትንና የማያስተምሩን መ ምሁራን አንተሙ ኢትበውኡወለእ ለሂ ይበውኡ ትከልእዎሙ በዊአ »

«እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እን ዳይገቡ ትከለክሏቸዋላችሁ» ብሏቸዋል ማቴ 23፡ 13 ስለ ምእመናን ችግር የማ ያስቡ ከሆነ የራሳቸውንም ችግር አያስ ተውሉም ስለዚህ ሁላችንም መታመን ይኖርብናል ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ

---

## የሥጋ ደዌ ...

ከገፅ ፲፱ የዞረ

ውን ደብቀው ከተባባሰ ደረጃ በማድረ ሳቸው የሚያጋጥማቸው ችግር ይህ ብቻ አይደለም ። ሌሎች ሰዎች ከእነር ሱ ጋር መሥራት ፡ መነጋገርና አብሮ መብላት ስለማይፈልጉና ገለልተኛ ስለ ሚያደርጋቸው ከባድ የአእምሮ ጭንቀ ትና ሃዘን ይሰማቸዋል ።

ስለዚህ ይህ በሽታ የያዛቸው ሰዎች በቶሎ ወደ ሕክምና ባለሙያዎች ቢቀ ርቡ በሽታው አስከፊ ከሆነ ደረጃ ላይ ሳይደርስ ጭንቀትና ሀዘንም ሳይፈጠር፡ እነርሱም ሆኑ ሐኪሙ ብዙ ልፋትና ድካም ሳያጋጥማቸው ሌላው ኅብረተሰ ብም ሳይበከል በሽታውን ጨርሶ ማጥ ፋት ይቻላል ። ሌላው ችግር ይህ በሽታ እንደሌሎች በሽታዎች የሚገድል ሳይ ሆን ለዕድሜ ልክ አብሮ የሚኖር በመ ሆኑ እጅና እግር ከተቆራረጠ መሥራት ስለማይቻል ወደ ልመና በመሠማራት የሀገርና የወገን ሸክም መሆንን ማስከ ተሉ ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስም በሐዋ. ሥራ ም. 20 33-35 እንዲህ በማለት ይናገራል ።

ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላ ችሁ ። እንዲሁ እየደከማችሁ ድውዮ ችን ትረዱና እርሱ ራሱ ከሚቀበል ይል ቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘን ድ በሁሉ አሳየኋችሁ ። እንግዲህ ይህን ሁሉ በመረዳት እያንዳንዱ ቢያንስ እን ኳ ራሱንና ቤተሰቡን ለመርዳት የሚ ቻል ከሆነም ለሌሎች ለማትረፍ የበቃ ይሆን ዘንድ የመላ አካሉን ጤንነት መ ንከባከብ ይኖርበታል ።

ነርስ ተማሪ የሺሐረግ ሥርጋዊ

## ምን እንርዳዎ?

ከገፅ ፲፰ የዞረ

ይህም ይታወቅ ዘንድ ሄሮድስ ያስገ ደላቸው ሕፃናት ሁለት ዓመት የሞላቸ ውን ነው ። ሄሮድስ ከሰብአ ሰገል ጠይ ቆ ኮከብ የታየበት ዘመን ሁለት ዓመት የመላው መሆኑን ስለተረዳ ክርስቶስም ሁለት ዓመት እንደሆነው በማወቅ የ ሁለት ዓመት ሕፃናትን በማስፈጀቱ ይ ታወቃል ማቴ. 2፡16

ሌሎቹ ሁለት ጥያቄዎችህ ግን በአካባ ቢህ ያሉ መምህራንን ጠይቀህ ልትረዳ ቸው የሚችሉ ተራ ጥያቄዎች በመሆና ቸው አላወጣናቸውም ።



---

# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅ ርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀ ረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመ ረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org



ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት የተጻፉ   ብራናው በዚህ መልክ እየተሠራ ነው ።

# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ደ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢ.ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org